በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ ፣ አያያዝ እና አጠቃቀምን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት

/FOLLOW UP AUDIT/ ሪፖርት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)(Executive summary) i
ክፍል አንድ 1
መግቢያ 1
የክትትል ኦዲቱ ዓላማ 2
የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 3
የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 4
ክፍል ሁለት 5
በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች 5
ኤጀንሲው የጡረታ ፈንድን አስመልክቶ የወጣውን አዋጅና 5
ደንብ መሰረት አድርጓ መመሪያ ማውጣቱን በተመለከተ፤ 5
ሰራተኞች ብዛት ለማወቅ ያጠናው ጥናት መኖሩን በተመለከተ፣ 8
ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅዱ መሸፈን ያለባቸው የግል ድርጅቶችና 9
ሠራተኞች እንዲሸፈኑ ማድረጉን በተመለከተ 9
ኤጀንሲው የግል ድርጅቶች በአዋጁ መሰረት በየወሩ እንዲከፍሉ ማድረጉንና 11
ስለመክፈላቸውም የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤ 11
የሚሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ሂሳብ በኤጀንሲው ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ 20
አካላት በአዋጁ መሰረት በትክክል ገቢ ሊያደርጉ፣ ኤጀንሲውም በውሉ መሰረት 20
እየሰሩና በትክክል ገቢ ማድረጋቸውን መከታተሉን በተመለከተ፣ 20
ኤጀንሲው ግዴታቸውን በማይወጡ የግል ድርጅቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ 28
የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋና ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ 28
ኤጀንሲው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን በመሰብሰብና 31
የሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ የጡረታ መዋጮ ገቢ ማቀዱንና 31
አጠቃላይ የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ መዘጋጀቱን በተመለከተ፤ 31
ኤጀንሲው ትርፋማነታቸው በተረጋገጠ ኢንቨስትመንቶች ላይ በመሰማራትፈንዱን ማዳበሩን በተመለከተ፤ 33
ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ ፈፃሚ አካላትንና ባለድርሻ አካላትን ማሳተፉን፣ 36
የተቋማቱን አቅም ለማጐልበት ስልጠና መስጠቱን እንዲሁም በኤጀንሲው 36
የሚሰጡ አገልግሎቶችን በመገምገም ግብረ መልስና ሙያዊ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፤ 36
ኤጀንሲው አገልግሎቶቹን በተጠናከረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርአትና የጡረታ ፈንዱን 40
የሚመለከቱ ማስረጃዎች በተሟላና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ አደራጅቶ መያዙን በተመለከተ፤ 40
ኤጀንሲው ለተገልጋዮችና ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ 43

መስጠቱንና በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለይቶ የሚፈታበት..43
ወጥ የሆነ መደበኛ የውይይት መድረክ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤..43
ክፍል ሦስት 46
የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)... 46
3.1እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው 46
3.2እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው 46
ክፍል አራት... 49
የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation) 49
አባሪ 1..i
አባሪ 2...ii
አባሪ 3...VII

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)

(Executive summary)

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2006/2007 ዓ.ም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ አሰባሰብ፣ አስተዳደ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ፣ አስተዳደርና አከፋፈል ብቃት ያለው ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ፤ እንዲሁም ኤጀንሲው የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በደብዳቤ ቁጥር ገፈ5.2/2/43/08 የካቲት 29 ቀን 2008 ዓ.ም. ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው ፡-

- ✓ ኤጀንሲው በክዋኔ ኦዲት ወቅት የተገኙ ክፍተቶችን እና የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦችን ሪፖርት ለሚመለከታቸው የሪጅን እና የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ሃላፊዎች አለማሳወቅ፣
- ✓ በኤጀንሲው የግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ አለመቋቋሙ፣
- ✓ በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ በማህበራዊ ዋስትና የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞች ብዛትን ለማወቅ የሚያስችል በኤጀንሲው የተጠና ጥናት አለመኖሩ፣
- ✓ ኤጀንሲው እያንዳንዱ የግል ድርጅት የሠራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደመወዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ በየወሩ በትክክል ስለመክፈሉ እስከ ወረዳ ድረስ የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት የተዘረጋ ውጤታማ የአሰራር ስርአት የሌለው መሆኑ፣
- ✓ ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅዱ የተሸፈኑ የግል ድርጅቶችን አዋጁ ባስቀመጠው መሰረት በተሟላ ሁኔታ በየወሩና በትክክል እንዲከፍሉ ያላደረገ መሆኑ፣
- ✓ የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ሂሳብ በኤጀንሲው ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ አካላት በአዋጁ መሰረት በትክክል ገቢ ማድረጋቸውን እና በውሉ

መሰረት እየሰሩ ስለመሆኑ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር በበቂ ደረጃ አለመደረጉ፣

- ✓ በኤጀንሲው ከግል ድርጅቶች ተሰበሰበው ወደ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወቅቱ ሳይተላለፉ የሚዘገዩ እና ከየት እንደተሰበሰቡ የማይታወቁ የጡረታ መዋጮ ሂሣቦች መኖራቸው፣
- ✓ ወጥ የሆነ የጡረታ መዋጮ አሰባሰበ የሌለ መሆኑ (በአዲስ አበባ ውክልና በተሰጣቸው የገቢ ሰብሳቢ ጽ/ቤቶች ሲሰበሰብ በሪጅንና ቅ/ጫ/ጽ/ቤች ደግሞ የግል ድርጅቶቹ የጡረታ መዋጮ ሂሳባቸውን ራሳቸው በቀጥታ ወደ ጡረታ መዋጮ ባንክ አካውንት የሚያስገቡ መሆኑ)፣
- ✓ ጡረታ መዋጮ ፈንዱን ለማዳበር የጡረታ መዋጮውን አሚጦ በመሰብሰብ ትርፋማ እና ውጤታማ በሆኑ ኢቨንስትመንቶች ላይ ለማዋል በጥናት ላይ የተመሰረተ እቅድ አለመኖሩ፣
- ✓ ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ገቢን ሲያቅድ የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን በመሰብሰብና የሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ ሳይሆን በግምትና የጡረታ መዋጮ በየዓመቱ ስለሚጨምር ይጨምራል በሚል መነሻ መሆኑ፣
- ✓ ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮውን ለማዳበር በወቅቱ አሚጦ የማይሰበስብ መሆኑ እንዲሁም የጡረታ ፈንዱንም በትሬዠሪ ቦንድ ሽያጭ ላይ ብቻ የሚያውልና ሌሎች አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች በማዋል በተጨማሪ ማግኘት ያለበትን ትርፍ እያገኘ አለመሆኑ፣

እስካሁን መኖሩ ታውቋል፡፡

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራም የተጀመረው እ.አ.አ ከ1883 እስከ 1889 የጀርመን ገዥ በነበረው ቻንስለር ቢስማርክ ዘመን እንደሆነ ይነገራል፡፡ ፕሮግራሙ በአገሮች ላይ የሚከሰተውን የኢኮኖሚም ሆነ ማህበራዊ ቀውስ መፍቻ አንድ መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የማህበራዊ ዋስትና የዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ የዓለም ሥራ ድርጅት እ.አ.አ በ1952 ባወጣው ደንጋጌ ቁጥር 102/1952 አገሮች እንደ ራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ዜጎቻቸውን የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን ተጠቃሚ ማድረግ እንዳለባቸው ደንግጓል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ሠራተኞችን በድንገት ከሚደርስባቸው የሥራ ላይ አደጋ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ከሥራ በሚሰናበቱበት ወቅት የሕይወት ምስቅልቅል እንዳይከሰት እየታደገ ይገኛል፡፡ በርካታ ሠራተኞችም የተረጋጋ ሕይወት እንዲመሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

2. በአገራችን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የሃገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ደረጃ በደረጃ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይደነግጋል፡፡ የትምህርት፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብ እና የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራም ሽፋን ማግኘትን በግልፅ በማስፈር፡፡ ይህንን ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ለማሳካት የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞችን ከ1953 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ ማደረግ የተጀመረ ሲሆን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቀጣሪዎች፣ የመከላከያና የፖሊስ አባላት ባለፉት 51 ዓመታት የማህበራዊ ዋስትና ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

3. በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድም የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎትን ማስፋፋትና የቁጠባ ባህልን ማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ ከፖሊሲና ከዕቅድ አኳያ ከተመለከትነውም አገሪቱ የማህበራዊ ደህንነት ልማት ፖሊሲ ትኩረት ከሠጣቸው ጉዳዮች አንዱ የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞችን የማስፋፋትና የማጠናከር ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህም ዋንኛው ምክንያት በአሁኑ ወቅት በተጨባጭ አብዛኛው የሀገሪቱ ዜጋ ተቀጥሮ በመስራት ላይ ያለው በግሉ

መደበኛ ክፍለ ኢኮኖሚ በመሆኑና ይህም በቀጣይ እየጨመረ ለመሄዱ አመላካች ነገሮች በመኖራቸው መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 202/2003 ዓ.ም. አቋቁሟል፡፡ ይህን ዘርፍ በይበልጥ ለማጠናከር ብሎም ተቀጥረው የሚሰሩ ሠራተኞችን የማህበራዊ ዋስትና መብት ለማረጋገጥ ሲባል በአዋጅ ቁጥር 715/2003 እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ መሠረት ሁሉም አንድና ከአንድ በላይ ሠራተኛ ቀጥረው የሚያሠሩ የግል ድርጅቶች በጡረታ ሥርዓቱ የመመዝገብና ሠራተኞቻቸውንም የማስመዝገብ እንዲሁም በአዋጅ የተቀመጠውን የጡረታ መዋጮ መጠን ወቅቱን ጠብቀው መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡

4. የግል ድርጅቶች ማለት በአዋጁ እንደተገለጸው በእርሻ፣ በኢንዱስትሪ፣ በንግድ፣ በአገልግሎት፣ በኮንስትራክሽን እና ሌሎች ለህጋዊ ዓላማ የተቋቋሙ ድርጅቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን የበጎ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትንም ይመለከታል፡፡ ኤጀንሲው በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የግል ድርጅቶች ሠራተኞችን የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን መብት ለማረጋገጥ በምዝገባና መረጃ ማደራጀት፣ በጡረታ መዋጮ ገቢ አሰባሰብ፣ በፈንድ ኢንቨስትመንትና አስተዳደር እና በአቅም ግንባታ ሥራዎች ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

5. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2006/2007 ዓ.ም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ፣ አስተዳደርና አከፋፈል ብቃት ያለው ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ፤ እንዲሁም ኤጀንሲው የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በደብዳቤ ቁጥር ገፈ5.2/2/43/08 የካቲት 29 ቀን 2008 ዓ.ም. ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ

ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

6. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው ከ2007-2009 ዓ.ም ያሉትን የሶስት በጀት ዓመታት የሥራ ክንውኖችን እንቅስቃሴ መሰረት ባደረገ በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ፣ አስተዳደርና አከፋፈል ብቃት ያለው ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ላይ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን እና ኤጀንሲው እነዚህን የኦዲት ግኝቶች የሚፈታበት የኦዲት ግኝት ማሻሻያ ሃሳቦች የሚተገበሩበትን የማሻሻያ እርምጃ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ባቀረበው መሰረት የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች በተዘጋጀው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት መተግበራቸውን እና ችግሮቹ መቀረፋቸውን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲቱ እስከተከናወነበት እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በኤጀንሲው የተከናወኑ ስራዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

7. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ዋና መ/ቤት እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመረጠው ከታዩ ሪጅን ፅ/ቤቶች መካከል የደቡብ ሪጅን ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና የሰሜን ምዕራብ የሪጅን ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ ከቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መካከል የሰሜን አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ የደቡብ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ የምስራቅ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ የሆሳዕና ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ የደብረማርቆስ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ፣ የጡረታ አበል ሰብሳቢ ተቋማት መካከል የሆሳዕና ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን፣ የሀዋሳ ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን፣ የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት መካከል አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ደብረማርቆስ እና ባህርዳር ቅርንጫፍ እና አሰሪ መ/ቤቶች በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለክክትል ኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ነው፡፡

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

8. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች

ኤጀንሲው የጡረታ ፈንድን አስመልክቶ የወጣውን አዋጅና ደንብ መሰረት አድርጓ መመሪያ ማውጣቱን በተመለከተ፤

9. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

በኤጀንሲው የግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ በየወሩ እንዲከፍሉ የሚያደርግ አስገዳጅ ህግና የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ የሚቋቋምበት የህግ ማዕቀፍ፣ የፈንድ አስተዳደር ማንዋል የሌለ መሆኑ እንዲሁም በኤጀንሲው የሂሣብ አያያዝ ማንዋል በረቂቅ ደረጃ ቢኖርም በሚመለከተው አካል ታይቶ እንዲጸድቅ አለመደረጉ፣

በጡረታ አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 13 ቁጥር 1/ለ ላይ የጡረታ ፈንዱ ለትሬዠሪ ቦንድ መግዣና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ለሚወሰኑ ሌሎች አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች ላይ ይውላል የሚል ቢሆንም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር መመሪያውን ባለማውጣቱ ኤጀንሲውን አስተማማኝ የማህበራዊ ዋስትና ተቋም እንዲሆን ለማድረግና የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር ከትሬዠሪ ቦንድ በተጨማሪ አዋጭና አስተማማኝ በሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ኢንቨስት እንዳያደረግ ተጽእኖ ያደረገ መሆኑን፣

እንዲሁም በየወሩ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ የሚጣል ቅጣት ባለመኖሩ የግል ድርጅቶቹ ትኩረት ሰጥተው በየወሩ የማይከፍሉ ሲሆን በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ወይም ንብረት ይዞ ለመሸጥ /ህጉን ለማስፈጸም/ የጨረታ ኮሚቴ የሚቋቋምበት የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ ችግር የፈጠረ እንደሆነ ተገኝቶ ነበር፡፡

10. ኤጀንሲው የግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ በየወሩ እንዲከፍሉ የሚያስችል አስገዳጅ ህግ ሊያወጣና በትክክል በአዋጁ መሠረት ስለመክፈላቸው እስከ ወረዳ ድረስ የሚወርድ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

11. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፈ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት

ጸድቆ በነጋሪት ጋዜጣ ሲታተም መመሪያው እስከ ሰኔ 30, 2007 ዓ.ም ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ገልጿል፡፡

12. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

13. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑን፣ የጡረታ መዋጮ ለማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ተመድቦ ክትትል እንደሚያደርግ እና ከአቅማቸው በላይ የሆነ ነገር ካለ ወደ ሪጅን ፅ/ቤት ነው የሚላክ መሆኑን፣

14. በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑን ፣ የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ጉዳዩን ለህግ ክፍል በማሳወቅ ከአካውንታቸው እንዲቀነስ እንደሚደረግ፣

15. በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑን፣ የጡረታ መዋጮ የማይከፍሉ ድርጅቶችን ለአዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት የሚያሳውቁ መሆኑን እና እስካሁን ንብረት ይዘው ያልሸጡ መሆኑን፣

16. በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑን እና ለጨረታ ኮሚቴ የህግ ማዕቀፍ የሌለ መሆኑን፣

17. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑን እና የህግ ማዕቀፍ ግን ያለ መሆኑን፣

18. በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑን፣ የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ የማግባባት ስራ ከተሰራ በኋላ ወደ ህግ የሚሄዱ መሆኑን፣

19. በሰሜን ምዕራብ ሪጅን የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ ያልተቋቋመ ሲሆን የህግ ማዕቀፍ ግን ያላቸው መሆኑን ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

20. ኤጀንሲው የጡረታ ፈንዱን ከትሬዠሪ ቦንድ መግዣ በተጨማሪ በሌሎች አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች ላይ እንዲውል ማድረጉን በተመለከተ በአዋጁ መሰረት የጡረታ ፈንዱ በሌሎች አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች ላይ እንዲውል መመሪያ የሚያወጣው የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መሆኑን እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርን የአዋጅ ማሻሻያ የሚፈቀድ ከሆነ በደብዳቤ የጠየቁ ቢሆንም ለጊዜው እንደማይቻል ምላሽ የተሰጣቸው መሆኑን ከኤጀንሲው ፈንድና ኢንቨስትመንት ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

21. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በክዋኔ ኦዲት በተሰጠው አስተያየት መሰረት ንብረት የሚያዝበት የሚሸጥበትና የጡረታ መዋጮ የሚሰበስብበት የአፈፃፀም ማኑዋል አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋሉን፣ በአፈጻጸም ማኑዋሉ አንቀፅ 15 /ንዑስ አንቀፅ 15.1 እና 15.2/ መሰረት ዉዝፍ የጡረታ መዋጮ አሠባሰብ /የጨረታ ኮሚቴ የሚኖረው በዋናው መ/ቤት እና በሪጅን ጽ/ቤቶች ብቻ ሲሆን በቅ/ጽ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ ለማስከፈል ንብረት መሸጥ ካስፈለገ ተፈፃሚ የሚሆነው በማኑዋሉ መሰረት በሪጅን ጽ/ቤቶች በተቋቋመው የጨረታ ኮሚቴ መሆኑን፣

22. በማኑዋሉ መሰረት የጨረታ ኮሚቴ አነማንን እንደሚያካትት የተቀመጠ ቢሆንም አባላቱ የሚሰየሙት የሚሸጠው ንብረት በህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ከተለየና ከተከበረ በኋላ እንደሆነ፣/አንቀፅ 15 /ንዑስ አንቀፅ 15.3/ ይህ እንዲሆን የተፈለገው አንድን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ለማስከፈል አንድ ኮሚቴ በማቋቋም በቋሚነት የሚሰሩ የኮሚቴ አባላት ቢሆኑ ሊያጋጥም የሚችለዉን የኪራይ ሰብሳቢነት /ሙስና/ስጋት ለመቅረፍ በአመራሩ ውይይት ተገርኀበትና ታምኖበት መሆኑን፣

23. የንብረት ሽያጭ የሚከናወነው ሌሎች መዋጮ የማስከፈያ አማራጮች /አዋጁ የተቀመጡት/ በአግባቡ ከተሟጠጡና ሌላ አማራጭ አለመኖሩ ሲረጋገጥና በበላይ አመራሩ ሲፈቀድ እንደሆነ እና የንብረት ሽያጭ አሉታዊ ተጽኖ እንዳይፈጠርና የመልካም አስተዳደር ችግር ምንጭ እንዳይሆን በጣም በተመጠን መልኩ የመፈጸም አቅጣጫን መከናወኑን፣

24. በዚሁ አግባብ በዋናው መ/ቤትና በሪጅን ጽ/ቤቶች የተወሰኑ አሰሪዎችን ንብረት የመሸጥና ያልተከፈለ መዋጮን ገቢ የማስደረግ ሥራ መሰራቱን እና በአብዛኛው

አሰሪዎች በህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ንብረት ሲታገድ /ሲከበር ወደ ሽያጭ ከመግባቱ በፊት ዕዳቸውን ስለሚከፍሉ ንብረት እስከ መሸጥ የሚያደርሱ ጉዳዮች ዉስን መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

25. ይሁን እንጂ የጨረታ ኮሚቴ ስለመቋቋሙ፣ በጨረታ ኮሚቴው አማካኝነት ንብረት ስለመሸጡ ለኦዲት ቡድኑ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

<u>ኤጀንሲው በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞች ብዛት ለማወቅ ያጠናው ጥናት መኖሩን በተመለከተ፣</u>

26. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

27. በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ በማህበራዊ ዋስትና የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞችን ብዛት ለማወቅ በኤጀንሲው የተጠና ጥናት አለመኖሩ ተገኝቶ ነበር፡፡

28. በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ በማህበራዊ ዋስትና የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞች ብዛት ለማወቅ በአዲስ አበባም ሆነ በክልሎች በክልላቸው ባለው ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት እንዲያጠኑ ወይም አንድ ኮሚቴ በማቋቋም ወደ ክልል ድረስ ወርዶ እንዲያጠና በማድረግ መረጃ ሊኖረውና ዕቅድ ሲያቅድ መረጃውን መነሻ በማድረግ ሊያቅድ እንዲሁም በየጊዜው መረጃው ካላቸው አካላት /ከኢንቨስትመንት፣ ከንግድ ኢንዱስትሪ…/ ኤጀንሲው መረጃ በማምጣት ወቅታዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

29. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፈ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በ 2008 በጀት ዓመት እንደሚጠናቀቅ ገልጿል፡፡

30. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

31. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት ፣ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት፣ በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት እና በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ በማህበራዊ ዋስትና የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞችን ብዛት ለማወቅ በኤጀንሲው የተጠና ጥናት የሌለ መሆኑን እና አሁን እየሰሩ ያሉት ከስታትስቲክስ ኤጀንሲ እና ከግብር ከፋዮች መረጃ በመነሳት እንደሆነ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

32. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ኤጀንሲው በክዋኔ ኦዲት በተሰጠው አስተያየት መሰረት ጥናቱን ለማከናውን በ2008 ዓ.ም ዓቅዶ የነበረ ቢሆንም ጥናቱ ሊሸፍነው ከሚገባው አገራዊ የቆዳ ስፋትና የግል ድርጅቶች ብዛትና ስርጭት አንጻር ሲታይ የሚጠይቀው ጊዜ የሰው ሀይልና የፋይናንስ/በጀት/አቅም በጣም ከፍተኛ በመሆኑ አሁን ባለው የኤጀንሲው አቅም አገር አቀፍ ጥናት (survey) ለማድረግ ተጨማሪ ዝግጅት የሚጠይቅና በዘርፉ ከተሰማሩ ድርጅቶች /ለምሳሌ ከማእከላዊ ስታቲክስ ኤጀንሲ/ ሙያዊ ድጋፍ ለማግኘት በቅንጅት መስራትን የሚጠይቅ በመሆኑ በተሰጠው አስተያየት ለመፈፀም ሠፋ ያለ ጊዜና ዝግጅት የሚጠይቅ እንደሆነ፣

33. ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው በራሱ የተከናወነ አገር አቀፍ የግል ድርጀቶችና ሠራተኞችን ብዛትና ስርጭት የሚያሳይ ጥናት ባይኖረዉም ከማዕከላዊ ስታቲክስ ኤጀንሲ ከንግድ ሚኒሲተርና ከኢንቨስትመንት ኮሞሽን የግል ድርጀቶች መረጃዎችን በማሰባሰብ አገራዊ የኢኮኖሚ /በተለይ የኢንዱስትሪ መስፋፋት/ እና በተጨባጭ ባለፉት አመታት ያለዉን የአፈፃፀም አዝማሚያ (trend) ከግምት በማስገባት በዚሁ ላይ ተመስርቶ ስትራቴጂክና ዓማታዊ ዕቅድ እያቀደ ተግባረዊ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

<u>ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅዱ መሸፈን ያለባቸው የግል ድርጅቶችና ሠራተኞች እንዲሸፈኑ ማድረጉን በተመለከተ</u>

34. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

35. ኤጀንሲው በስትራቴጂክ ዕቅዱ እስከ 2007 ዓ.ም. 119,700 የግል-ድርጅትና 880,000 የግል-ድርጅት ሠራተኞች ለመመዝገብ ያቀደ ሲሆን ነገር ግን የ2004 በጀት አመት በእቅድ ያልተቀመጠ ሲሆን በ2005 ዓ.ም 69,300፣ በ2006 ዓ.ም 36,564 የግል ድርጅት ለመመዝገብ የታቀደ ቢሆንም ዕቅድ አፈጻጸሙ ሲታይ በ2004 ዓ.ም. 20,170 ፣ በ2005 ዓ.ም. 42,004 /60%/፣ በ2006 ዓ.ም 18,859/52%/ ብቻ መመዝገቡን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በሁለቱ ዓመት መመዝገብ ሲገባቸው ያልተመዘገቡ 45,001 ድርጅቶች ያሉ ሲሆን በአጠቃላይ እስካሁን በስትራቴጂክ ዕቅዱ ለመመዝገብ ከታቀደው 119,700.00 የግል-ድርጅቶች 81,033/68%/ የተመዘገቡ ሲሆን 38,667/32%/ ያልተመዘገቡ መሆናቸውን ከኤጀንሲው በተገኘ

ማስረጃ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን እንዲሁም በሆሳዕና ቅ/ጫ/ጽ/ቤት በ2006 ዓ.ም. 3000 ሠራተኛ ሊመዘግቡ አቅደው ነገር ግን 1,854 ሠራተኛ ማለትም 60 በመቶ ብቻ የመዘገቡ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

36. ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅድ መሸፈን ያለባቸውን ሠራተኞችና የግል ድርጅቶች የተለያዩ ግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶችን በማዘጋጀት የጡረታ መዋጮ ጠቀሜታ ላይ ግንዛቤው ሊሰጥና የሪጅንና ቅ/ጫ/ጽ/ቤቶችን አቅም በማሳደግ የግል-ድርጅቶቹ በራሳቸው ተነሳሽነት በዐቅዱ እንዲሸፈኑ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር።

37. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፊ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር እስከ ሰኔ 30, 2007 ዓ.ም ድረስ በስትራቴጂክ ዕቅድ የተቀመጠውን ግብ ማሳካት እንዳለበት ገልጿል፡፡

38. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

39. በደቡብ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ 2007 ዓ.ም 1,704 ድርጅቶችን እና 12,288 ለመመዝገብ ታቅዶ አፈፃፀሙ 1,104 (64.8%) ድርጅቶች እና 5,854 (47.64%) ሰራተኞችን የመዘገበ መሆኑን ከእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

40. በምስራቅ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ 2007 ዓ.ም 2,124 ድርጅቶችን እና 12,696 ሰራተኞችን ለመመዝገብ ታቅዶ አፈፃፀሙ 1,358 (64%) ድርጅቶች እና 6,171 (48.6%) ሰራተኞችን የተመዘገቡ እንደሆነ፣ እና በአዲስ አበባ ቁጥር 2 ቅርንጫፍ ፅ/ቤት መሰራት የነበረባቸው የምዝገባ ስራዎች በተለያዩ ምክንያቶች ቀድመው ባለመሰራታቸው አጠቃላይ የፅ/ቤቱ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩን እንዲሁም የድጅትና የሰራተኞ አቅድ አባልነት ካርድ ወዲያውኑ መሰጠት ያለመቻሉን ከእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. በሰሜን አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ 2007 ዓ.ም 1,944 ድርጅቶችን እና 12,060 ለመመዝገብ ታቅዶ አፈፃፀሙ 972 (50.%) ድርጅቶች እና 3,927 (31.17%) ሰራተኞችን የመዘገበ መሆኑን ከእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት፣ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት፣ በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት እና በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ከሐምሌ 2003 ዓ.ም በፊት የተቋቋመ የግል ድርጅት በፕሮፊደንት ፈንድ መቀጠል የሚችል እንደሆነ እና ከሰኔ 17/2003 ዓ.ም በኋላ

የተቋቋመ የግል ድርጅት ወደ ጡረታ ዐቅዱ እንዲገባ የተደረገ መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

43. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በፅ/ቤቶች መካከል የአፈፃፀም ልዩነት /ከፍና ዝቅ ያለ አፈፃፀም/ ቢኖርም የዋናው መ/ቤትና የጽ/ቤቶች እንደ ኤጀንሲ ተጠቃሎ ሲታይ በስትራቴጂክ ዘመኑ የነበረው የድርጅቶችና የሰራተኞች ምዝገባ ዕቅድ አፈፃፀም በስትራጂክ ዕቅዱ ከተቀመጠው አንፃር መሆኑን፣ የታቀደ የድርጅት ምዝገባ 119,700 ሲሆን የተፈፀመ 111,289 ወይም በመቶኛ 93% ፣ የሰራተኛ ምዝገባ 880,000 ሲሆን 850,713 ወይም በመቶኛ 97% መሆኑን ገልፀዋል፡፡

44. ይሁን እንጂ የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች የገለፁት አፈፃፀም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

ኤጀንሲው የግል ድርጅቶች በአዋጁ መሰረት በየወሩ እንዲከፍሉ ማድረጉንና ስለመክፈላቸውም የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

45. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

46. ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅዱ የሚሸፈኑ የግል ድርጅቶችን አዋጁ ባስቀመጠው መሰረት በየወሩና በትክክል እንዲከፍሉ ያላደረገ በመሆኑ ከ3 ወር እስከ ሁለት አመትና ከሁለት አመት በላይ የማይከፍሉ ድርጅቶች መኖራቸውን፣

47. በሀገሪቱ ባሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ሥር ያሉ የትራንስፖርት ባለሙያዎች የሥራ ግብር በቁርጥ በአመት አንዴ በመክፈላቸው የጡረታ መዋጮ ማስከፈል አለመቻሉን፣

48. ኤጀንሲው የግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ በየወሩ እንዲከፍሉ የሚያስችል አስገዳጅ ህግ ሊያወጣና በትክክል በአዋጁ መሠረት ስለመክፈላቸው እስከ ወረዳ ድረስ የሚወርድ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

49. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፈ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር የኤጀንሲውን የጡረታ መዋጮ መከታተያ ስርዓት በማጠናከር የእያንዳንዱን ድርጅት መረጃ በሌጀር

እየተመዘገበና እየተረጋገጠ እንዲያዝ በማድረግ ላይ መሆናቸውን፣ ስራዎቹን በመረጃ ቴክኖሎጂ ለማስደገፍ ጥናቱን አጠናቆ መረጃዎችን ወደ አዲሱ ሲስተም የማስገባት ስራ እስከ ታህሳስ 2008 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ ገልጿል፡፡

50. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

51. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅዱ የሚሸፈኑ የግል ድርጅቶች ለሰራተኛው በሚከፍለው መደበኛ የወር ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሰራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደሞዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ ለጡረታ ፈንዱ በየወሩ እንዲከፈል እንደሚያደርግ እና የሚያስከፍሉትም ከገቢዎች የስራ ግብር የተከፈለበት ፔሮል በመውሰድ እንደሆነ ፣ የጡረታ መዋጮ በየወሩና በአዋጁ መሠረት በትክክል ስለመከፈሉ የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት በመዘርጋት በሁሉም ሪጅንና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ የተዘረጋው ስርዓትም ከፌዴራል ገቢዎች ዳታ ኢንኮደር የግል ድርጅቶችን ሌጀር በማምጣት በመጣው ሌጀር ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ ሲሆን የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ስር ያሉ የትራንስፖርት ባለሞያዎች የጡረታ መዋጮ በአግባቡ የሚከፍሉ መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

52. ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት አብዛኞቹ የግል ድርጅቶች ግብር ሊከፍሉ ሲመጡ የጡረታ መዋጮ የሚከፍሉ መሆኑን፣ ገቢዎች ባለስልጣን ላይ የኤጀንሲው ሰራተኞች በማስቀመጥ ከስራ ግብር ፔሮል ጋር ልዩነቱን በማጣራት እንደሚሰበሰብና ልዩነት ከተፈጠረ ኦዲት እንደሚደረግ የጡረታ መዋጮ በየወሩና በአዋጁ መሠረት በትክክል ስለመከፈሉ የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት የገቢዎች የስራ ግብር የሚከፈልበት ፔሮል እንደሆነ፣የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ስር ያሉ የትራንስፖርት ባለሞያዎች የስራ ግብር የሚከፍሉት በዓመት አንድ ጊዜ በቁርጥ የሥራ ግብር በመሆኑ የጡረታ መዋጮ አሰባሰብ ላይ ክፍተት የፈጠረ በመሆኑ ለመቆጣጠርም አስቸጋሪ እንደሆነ እና ትራንስፖርት ዘርፍ ላይ ብዙ የጡረታ መዋጮ የማይከፍሉ የትራንስፖረት ዘርፍ ባለሞያዎች መኖራቸውን፣ የግል ድርጅቶች ለሰራተኛው በሚከፍለው መደበኛ የወር ደመወዝ ላይ ከአሰሪ የሠራተኛውን 7% እና የአሰሪዎችን 11% ቀንሰው እንዲከፍሉ እየተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

53. በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የግል ድርጅቶች ለሰራተኛው በሚከፍለው መደበኛ የወር ደመወዝ ላይ ከአሰሪ የሠራተኛውን 7% እና የአሰሪዎችን 11% ቀንሰው እንዲከፍሉ እንደሚደረግ፣ የጡረታ መዋጮ በየወሩና በአዋጁ መሠረት በትክክል ስለመክፈሉ የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት ከገቢዎች በሚያመጡት ሌጀር መሆኑን፣የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ስር ያሉ የትራንስፖርት ባለሞያዎች የስራ ግብር የሚከፍሉት በዓመት አንድ ጊዜ በቁርጥ የሥራ ግብር በመሆኑ ያልተሰራበት መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

54. በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት በጡረታ ዐቅዱ የሚሸፈኑ የግል ድርጅቶች ለሰራተኛው በሚከፍለው መደበኛ የወር ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሰራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደሞዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ ለጡረታ ፈንዱ በየወሩ እንዲከፍል እንደሚያደርጉ እና የጡረታ መዋጮ በየወሩና በአዋጁ መሠረት በትክክል ስለመክፈሉ የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት የግል ድርጅቶችን ኦዲት በማድረግ እንደሆነ ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ሥር ያሉ የትራንስፖርት ባለሙያዎችን በተመለከተ የጡረታ መዋጮ እየሰበሰቡ መሆኑን፣ ከትራንስፖርትና መገናኛ ቢሮ በደብዳቤ በማሳወቅ የጡረታ መዋጮ ያልከፈሉ በየዓመቱ ቦሎ ስለማይሰጣቸው እየከፈሉ መሆናቸውን ፣ በዞናቸው የአዲስ አበባ የሰሌዳ ቁጥር ያላቸው ነገር ግን በሆሳዕና የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡት ቦሎ የሚያመጡት ከአዲስ አበባ ስለሆነ የጡረታ መዋጮ መሰብሰብ እንዳልተቻለ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ታውቋል፡፡

55. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት በጡረታ ዐቅዱ የሚሸፈኑ የግል ድርጅቶች ለሰራተኛው በሚከፍለው መደበኛ የወር ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሰራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደሞዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ ለጡረታ ፈንዱ በየወሩ እንዲከፍል እንደሚያደርጉ እና የጡረታ መዋጮ በየወሩና በአዋጁ መሠረት በትክክል ስለመክፈሉ የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት የግል ድርጅቶችን ፔሮል በመመልከት እና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ እንደሆነ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ሥር ያሉ የትራንስፖርት ባለሙያዎችን በተመለከተ የጡረታ መዋጮ ካልከፈሉ ቦሎ ስለማይታደስላቸው እየከፈሉ መሆኑን፣ ነገር ግን ሙሉ

ለሙሉ ተመዝግበዋል ለማለት እንደማይቻል ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ታውቋል፡፡

56. በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት ከገቢዎች ባለስልጣን በሚያመጡት የደሞዝ መረጃ በመነሳት እንደሚሰሩ እና የጡረታ መዋጮ በየወሩና በአዋጁ መሠረት በትክክል ስለመክፈሉ የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት ከገቢዎች ባለስልጣን የደሞዝ ማስረጃ/ፔሮል/ በማምጣት እንዲሁም በሁሉም ወረዳዎች ላይ ባስቀመጧቸው ሰራተኞች ክትትል እና ቁጥጥር እንደሚያደርጉ፣

57. በአንድ ወር የከፈሉ የግል ድርጅቶች በሚቀጥለው ወር ስለመክፈላቸው ግን የሚያረጋግጡበት ስርዓት አለመኖሩን ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ስር ያሉ የትራንስፖርት ባለሞያዎች ላይ ክፍተት ቢኖርም የስራ በዓመት አንድ ጊዜ ለመክፈል ሲመጡ የጡረታ መዋጮውን ከነቅጣቱ የሚያስከፍሉ ቢሆንም በወቅቱ የማይከፍሉ እነደሆነ እና በወቅቱ እንዲከፍሉ የተዘረጋ ስርዓት የሌለ መሆኑን እንዱሁም የወር ደሞዛቸው ከ600 ብር በታች የሚከፈላቸውን እንዲከፍሉ ለማድረግ አለመቻሉን አሰባሰብ ላይ ክፍተት መፍጠሩን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቃለ-በጠይቅ ታውቋል፡፡

58. ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከተደረገላቸው ቃለመጠይቅ ምላሽ ለመረዳት እንደተቻለው በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት የግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ ከሰራተኛው ቀንሰው እና የራሳቸውን ጨምረው ለጡረታ ፈንዱ ገቢ እንደሚያደርጉ እና የጡረታ መዋጮ በየወሩና በአዋጁ መሠረት በትክክል ስለመክፈሉ የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት የግል ድርጅቶችን ኦዲት በማድረግ መሆኑን ነገር ግን የተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊ የማይደረግበት ወቅት መኖሩን፣ በሀገሪቱ ባሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ሥር ያሉ የትራንስፖርት ባለሙያዎች የጡረታ መዋጮ በአግባቡ እንዲከፍሉ የማድረጉ ስራ ላይ እንዳልገቡበት ታውቋል፡፡

59. የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ይሁን እንጂ በባህር ዳር የሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በየወሩና በአዋጁ መሠረት በትክክል ስለመክፈሉ የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት የሌለ መሆኑን፣

60. ለዚህም ማሳያ የሚሆነው በባህርዳር የሚገኘው ግራንድ ሆቴልና ስፓ የጡረታ መዋጮ ገቢ ከመጋቢት 2007 ዓ.ም እስከ ጥር 2009 ዓ.ም ድረስ የ 22 ወር

ያልተከፈለ የድርጅቱንና እና የሠራተኛውን የጡረታ መዋጮ ያልተከፈለ የጡረታ መዋጮ ገቢ ድምር 1,289,444.61 / አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ አራት መቶ አርባ አራት ብር ከስልሳ አንድ ሳንቲም/ ፣ እስካሁን ባልተከፈለ መዋጮ ገቢ ላይ ቅጣት ብር 613,144.55 / ስድስት መቶ አስራ ሶስት ሺ አንድ መቶ አርባ አራት ብር ከ ሃምሳ አምስት ሳንቲም/ ፣

61. እስካሁን ባልተከፈለ መዋጮ ገቢ ላይ ወለድ ብር 51,098.26 / ሃምሳ አንድ ሺ ዘጠና ስምንት ብር ከ ሃያ ስድስት ሳንቲም/ በአጠቃላይ ድምር ብር 1,953,684.45 / አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሶስት ሺ ስድስት መቶ ሰማንያ አራት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/ ውዝፍ እዳ እንዳለበት እና ማስረጃ ባለማቅረብ ክስ የመሰረተ ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ በግራንድ ሆቴልና ስፓ በአካል በመገኘት ባደረገው ማጣራት ኤጀንሲው ገቢ አልተደረገም ያለው ብር 1,289,444.61 / አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ አራት መቶ አርባ አራት ብር ከስልሳ አንድ ሳንቲም/ ገቢ የተደረገ መሆኑን በማስረጃ ያጣራ ሲሆን ቅጣት እና ወለድ ድምር ብር 664,239.84 / ስድስት መቶ ስልሳ አራት ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሰማንያ አራት ሳንቲም/ ገቢ እንዳልሆነ የኦዲት ቡድኑ ለማጣራት ችሏል፡፡

62. በባህር ዳር ሰሜን ምዕራብ ሪጅን /ፅ/ቤት ኢ.ትዮጵያ መኮንን የመጠጥና ማከፋፈያ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሲያደርጉ በተለያዩ ወሮች የአሰሪውን ድርሻ ተነጥሎ የሰራተኛውን የጡረታ መዋጮ ሳይጨምር ግንቦት 2006 ዓ.ም ሰራተኛ ድርሻ 955.95 /ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አምስት ብር 95/100 ሳንቲም /፣ በነሀሴ 2006 ዓ.ም ሰራተኛ ድርሻ 867.04 ብ/ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከ4/100 ሳንቲም/፣ በመስከረም 2007 ዓ.ም 1,036.55 ብር /አንድ ሺ ሰላሳ ስድስት ብር ከ55/100 ሳንቲም / ፣

63. ህዳር 2007 ዓ.ም 1,568.14ብር /አንድ ሺ አምስት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከ14/100 ሳንቲም /፣ ጥር 2007 ዓ.ም 2,074.08 ብር /ሁለት ሺ ሰባ አራት ብር ከ8/100 ሳንቲም / ፣ መጋቢት 2007 ዓ.ም 2,331.04 ብር /ሁለት ሺ ሶስት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከ4/100 ሳነቲም / በድምሩ 8,832.80 /ስምንት ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ ሁለት ብር ከ88/100 ሳንቲም / ገቢ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

64. በባህር ዳር ሰሜን ምዕራብ ሪጅን /ፅ/ቤት ለሳትኮን ኮንስትራክሽን ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ሪፈራል ሆስፒታል ፕሮጀክት ከ01/05/2006 እስከ 30/03/2007 ድረስ

ከውዝፍ ቀሪ የጡረታ መዋጮ ብር 244,319.21 /ሁለት መቶ አርባ አራት ሺ ሶስት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከ21/100 ሳነቲም/ ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

65. በባህር ዳር ሰሜን ምዕራብ ሪጅን /ፅ/ቤት እያሱ አዳምጤ ህንፃ ተቋራጭ የተባለው ድርጅት የራሳቸውንና የሰራተኛውን ድርሻ በየወሩ ማስገባት ሲገባቸው ለእንቁ ፕሮጀክት ከሀምሌ 2006 ዓም እስከ ታህሳስ 2007 ዓ.ም 63,316.23 ብር /ስልሳ ሶስት ሺ ሶስት መቶአስረሳ ስድስት ብር ከ23/100 ሳንቲም/ ፣

66. ለእያሱ ኮንስትራክሽን ከሀምሌ 2006ዓ.ም -ታህሳስ 2007ዓ.ም 151,859.77 ብር / አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ አጠኝ ብር ከ77/100 ሳንቲም / በአጠቃላይ 215,173 ብር /ሁለት መቶ አስራ አምስት ሺ አንድ መቶ ሰባ ሶስት ብር እና ከጥር 2007 እስከ ጥቅምት 2008 ዓ.ም የጡረታ መዋጮ ገቢ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

67. በባህርዳር የግ/ድ/ሠ/ማ/ዋ/ኤ ሰሜን ምዕራብ ሪጅን ጽ/ቤት ሲራክና ቤተሰቦቹ ፕላስቲክና አባይ ምንጭ ሎጅ ከየካቲት 2008 እስከ ሐምሌ 2008 ዓ.ም ድረስ የጡረታ መዋጮ ገቢ ያላረገበት በጥቅምት ወር 2009 ዓ.ም ሲገባ የዘገየበት ቅጣትና ወለድ የየካቲት 2008 ዓ.ም ቅጣት ብር 3,788.20 ወለድ ብር 315.68፣ የመጋቢት 2008 ዓ.ም ቅጣት ብር 3,349.35 ወለድ ብር 279.11፣

68. የሚያዚያ 2008 ዓ.ም ቅጣት ብር 2,784.47 ወለድ ብር 232.04፣ የግንቦት 2008 ዓ.ም ቅጣት ብር 2,367.83 ወለድ ብር 197.32፣ የሰኔ 2008 ዓ.ም ቅጣት ብር 1,751.75 ወለድ ብር 145.48፣ የሐምሌ 2008 ዓ.ም ቅጣት ብር 1,240.91 ወለድ ብር 103.41 ጠቅላላ ድምር ብር 16,556.05 (አስራ ስድስት ሺህ አመስት መቶ ሀምሳ ስድስት ከ 05 ሳንቲም) ዉዝፍ ያልተሰበሰበ መሆኑን ከመረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

69. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ሀዋሳ ጨርቃ ጨርቅ አ/ማ በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000027435 የሚታወቀው ድርጅት ቀጥሮ ለሚያሰራቸው ሰራተኞች መክፈል ያለበትን የጡረታ መዋጮ ዋናውንና ቅጣትና ወለድ ጨምሮ በአጠቃላይ ብር 4,317, 619.18/አራት ሚሊየን ሶስት መቶ አስራ ሰባት ሺ ስድስት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከ18/100 ሳንቲም፣ በግብር መለያ ቁጥር 0000056023 የተመዘገበው ማውንት ኦሊቭ ት/ቤት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ብር 1,116,493.93 (አንድ ሚሊየን አንድ

መቶ አስራ ስድስት ሺ. አራት መቶዘጠና ሶስት ከ93/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

70. በግብር መለያ ቁጥር 0001517282 የተመዘገበው ያማር ካፌና ሬስቶራንት የተባለው ድርጅት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ብር 392,883.13/ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት ሺ. ስምንት መቶ ሰማኒያሶስት ብር ከ13/100 ሳንቲም፣ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ፣

71. በደቡብ ሪጅን /ፅ/ቤት በይርጋለም ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ 45 ድርጅቶች ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን፣ ደቡብ ሪጅን /ፅ/ቤት ለይርጋለዓም ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ከፃፈው ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል።

72. በአርባ ምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ተመዝግበው የሚገኙና ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ያለባቸው ድርጅቶች አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር ከሰኔ 01/2007 እስከ ጥቅምት 30/2009 ብር 2,205,884.77 (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምስት ሺ. ስምንት መቶ ሰማንያ አራት ብር ከ 77/100 ሳንቲም) ፤በርሄ ሀጎስ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/ግ/ማ ከግንቦት 01/2007 እስከ ታህሳስ 30/2008 ዓ.ም ብር 1,186,534,15 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት ሺ. አምስት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከ 15/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

73. ዲ.ኤም.ሲ. ኮንስትራክሽን /ሁምቦ አርባ ምንጭ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ከየካቲት/ ከ ከሚያዚያ 01/2007 እስከ ታህሳስ 30/2008 ዓ.ም ብር 423,675.11 (አራት መቶ ሃያ ሶስት ሺ. ስድስት መቶ ሰባ አምስት ብር ከ 11/100 ሳንቲም)፣ሳትኮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/ግ/ማ / ላሳክ ሳላይሽ መንገድ ስራ ፕሮጀክት/ ከየካቲት 01/2007 እስከ ታህሳስ30/2008 ዓ.ም ብር 2,595,667.66 (ሁለት ሚሊየን አምስት መቶ ዘጠና አምስት ሺ. ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከ 66/100 ሳንቲም) ፣

74. ሳትኮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/ግ/ማ /አ/ምንጭ ዩኒቨርስቲ ስፖርት ፊልድ ግንባታ ፕሮጀክት/ ከህዳር 01/2006 እስከ ታህሳስ 30/2008 ዓ.ም ብር 100,672.50 (መቶ ሺ. ስድሰት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከ 50/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

75. እንዲሁም ሳትኮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/ግ/ማ / ሳውላ ላሳክ ኮንትራት -1 መንገድ ስራ ፕሮጅክት/ ከመስከረም 01/2009 እስከ ጥር30/2008 ዓ.ም ብር 1,672,550.60 (አንዲ ሚሊዮን ስድሰት መቶ ሰባ ሁለት ሺ. አምስት መቶ ሀምሳ ብር ከ 60/100

ሳንቲም)፣ አኬር ኮንስትራክሽን ከ03/03//2007 እስከ 30/05/2009 ብር 1,620,076,66 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሺ ሰባ ስድሰት ብር ከ 66/100 ሳንቲም)፣

76. ናሩስ ባዮ ቴክኖሎጅ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከግንቦት01/2006 እስከ መስከረም30/2008 ብር 62,077.04(ስልሳ ሁለት ሺ ሰባ ሰባት ብር ከ04/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

77. ጂ.ዋይ.ቢ.ኤስ አግሮ ኢንዱስትሪ ከ30/10/2008 እስከ 30/05/2009 ዓ.ም ብር 18,843(አስራ ስምንት ሺ ስምንት መቶ አርባ ሶስት ብር)፣ ፍሊንት እስቶን አንጅነሪንግ /ዲላ ዩኒቨርስቲፕሮጀክት/ ከሰኔ01/2007 እስከ መስከረም 30/2009 ብር 1,813,552.81 (አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ አስራ ሶስት ሺ አምስት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር ከ 81/100 ሳንቲም)፣

78. እንዲሁም ፍሊንት እስቶን አንጅነሪንግ /ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ፕሮጀክት ከነሀሴ01/2007- እስከ ጥቅምት 30/2009 ብር 929,889.69 9 ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከ 69/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

79. ማይ ፌቦራይት ካፍና ሪሰቶራንት/ሀዋሳ/ ከመስከረም 01/2006 እስከ ጥቅምት 30/2009 ዓ.ም ብር 232,336.34 (ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ ሶስት መቶ ሰላሳ ስድሰት ብር ከ 34/100 ሳንቲም)፣ በሃላባ ያማረ ካፌና ሬሰቶራንት ከሀምሌ01/2008 እስከ ሰኔ30/05/20098 ዓ.ም ብር 392,883.13 (ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ ሶስት ብር ከ 13/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

80. በደቡብ ሪጅን /ፅ/ቤት በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0036723128 እና ሲው/sew/ ኢንፍራ እስትራክቸር ሊምትድ በሚል ንግድ ስያሜ የሚጠራው እና በሪጅን ፅ/ቤት ተመዝግቦ የሚገኝ የመንገድ ግንባታ ስራ ድርጅት በድርጅቱ ቀጥሮ ያሰራቸው ለነበሩ 415 ሰራተኞች ከየካቲት 01/2008 እስከ ሰኔ 30/2008 ድረስ ያለውን ጊዜ በድርጅቱ መክፈል የነበረበት የአምስት /5/ ወር የጡረታ መዋጮ ወለድና ቅጣት ጨምሮ ብር 4,709,699.87 /አራት ሚሊየን ሰባት መቶ ዘጠኝ ሺ ስድስት መቶ ሃያ ዘጠና ዘጠኝ 87/100 ሳንቲም/ ውዝፍ ዕዳ ያለበትና የስራ ውሉን አቋርጦ አካባቢውን ጥሎ የሄደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

81. በደቡብ ሪጅን /ፅ/ቤት ኢንተርፕራይዝ ሊሚትድ /ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ / በሚል የንግድ ስያሜ ተመዝግቦ የሚገኘው እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000034517 እና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ንግድ ሚኒስቴር አህመት አዶሊዝ ኬኤምሲ ጆይንት ቬንቸር በሚል የንግድ ስያሜ ተመዝግቦ የሚገኘው እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0005123671 የአገር አቋራጭ የመንገድ ስራ ድርጅቶች የሆኑት የጡረታ መዋጮ የተከፈለበት ፔሮል የባንክ ስሊፐ ጉድለት ያለባቸው መሆኑና ስራቸውን አጠናቀው አካባቢውን ለቀው የወጡ መሆናቸው እና መክፈል የነበረባቸውን የጡረታ መዋጮ እንዳልከፈሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

82. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ዱቄት አ/ማ በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000029055 የሚታወቀው ድርጅት ከሀምሌ 01/2007-ታህሳስ 30/2008 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ብር 342,916.96/ ሶስት መቶ አስራ አርባ ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ አስራ ስድስት ብር ከ96/100 ሳንቲም ውዝፍ ዕዳ ያለበት መሆኑን፣ ሂሩት መታሰቢ ጠቅ/ን/ሃላ/የተ/የግ/ ማህበር በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0038203652 የሚታወቀው ድርጅት ከግንቦት 01/2006-ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ብር 20,803,.27 (ሃያ ሺ ስምንት መቶ ሶስት ብር ከ27/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ኦርኪድ ቢዝነስ ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000039973 የሚታወቀው ድርጅት ከጥቅምት 01/2006- ጥቅምት 30/20089 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ብር 845,893.60 (ስምንት መቶ አርባ አምስት ሺ ስምንት መቶ ዘጠና ሶስት ብር ከ60/100 ሳንቲም) ውዝፍ ዕዳ ያለበት መሆኑን፣

84. በደቡብ ሪጅን ጽ/ቤት ሐሮኒ ኢንተርናሽናል ሆቴል ከሐምሌ 1/2005 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ያልተከፈለ የአሰሪ እና የሰራተኛ ድርሻ ጠቅላላ መዋጮ ቅጣትና ወለድን ጨምሮ 1,365,510.31 (አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ አምስት መቶ አስር ብር ከሰላሳ አንድ ሳንቲም) ዕዳ ያለበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

85. በደብረ ማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት ከሀምሌ 2008ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30/2009 ዓ.ም ከተለያዩ የግል ድርጅቶች ያልተሰበሰበ ብር 1,800,389.81 (አንድ ሚሊየን ስምንት መቶ ሺ ሶስት

መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ከ81/100 ሳንቲም) መኖሩን ለማወቅ ተችሏል ። ዝርዝሩ በአባሪ 1 ተያይዟል።

86. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቀደም ሲል የግል ድርጅቶች መዋጮ መክፈል አለመክፈላቸውን ለመከታተል በማኑዋል ሌጀር ላይ በመመዝገብ ክትትል ሲደረግ የነበረ መሆኑን፣ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ኤጀንሲው የምዝገባ የመዋጮ ገቢና የአበል ዉሳኔ ሲስተም አስጠንቶ መረጃ በማስገባት ሥራ ላይ መሆኑን፣ የእያንዳንዱ ድርጅት የመዋጮ መረጃ ወደ ሲስተሙ ገብቶ ሲጠናቀቅ የተኛው በወሩ እንደከፈለ የተኛው እንዳልከፈለ የተከፈለው ክፍያ በደሞዙ መሰረት እንደሆነ...ወዘተ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል እንደሆነ፣

87. በመሆኑም ኤጀንሲው በማኑዋል የእያንዳንዱን ወር የጡረታ መዋጮ ለማጣራትና ፈጣን ማስተካከያ ለማድረግ ቢፈልግ እንኳን ካለው የድርጅቶች ቁጥር አንፃር በሚፈለገው ደረጃ ዉጤታማ ለመሆን ስለሚያስችል ዘላቂ የሆነ በመረጃ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ሥረዓት እንዲኖረው በአንክሮ እየሰራ እንደሚገኝ፣

88. ከዚህ ጎን ለጎንም የጡረታ መዋጮ ኦዲት ስራን በማጠናከር በ2009 እስከ በጀት ዓመቱ ከተመዘገቡ ድርጅቶች ውስጥ 3 ፐርሰንት ያህሉን ኦዲት ያደረገ እንደሆነ፣ በ2010 ከተመዘገቡ ድርጅቶች 5 ፐርሰንት ያህሉን ኦዲት በማድረግ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በመስራት ላይ እንደሚገ እና የኦዲት ሽፋኑ በየዓመቱ አፈፃፀሙ እየታየ ከፍ እያለ እንዲሄድ አቅጣጫ መቀመጡን ገልፀዋል፡፡

የሚሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ሂሳብ በኤጀንሲው ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ አካላት በአዋጁ መሰረት በትክክል ገቢ ሊያደርጉ፣ ኤጀንሲውም በውሉ መሰረት <u>እየሰሩና በትክክል ገቢ ማድረጋቸውን መከታተሉን በተመለከተ፣</u>

89. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

90. የጡረታ መዋጮ ገቢ አሰባሰቡ ወጥ ያልሆነና ኤጀንሲው ውክልና ከሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ ጽ/ቤቶች በተዋዋለው ውል አንቀጽ 4 ቁጥር 1 ላይ ውክልና የተሰጠው ገቢ ሰብሳቢ አካል የጡረታውን መዋጮ ሂሳብ ይሰበስባል ቢልም በአዲስ አበባ ካሉ ገቢ ጽ/ቤቶች በስተቀር በደቡብና ሰሜን ምዕራብ ሪጅን፣

91. በደብረማርቆስ፣ በጎንደርና በሆሳዕና ቅ/ጫ/ጽ/ቤቶች ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ ጽ/ቤቶች እንዲሁም አዲስ አበባ ባሉ የወረዳ ገቢ ጽ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ ገቢውን

የማይሰበስቡና የግል ድርጅቶቹ ራሳቸው የጡረታ መዋጮ ሂሳባቸውን በቀጥታ ወደ ባንክ ለጡረታ መዋጮ ተብሎ ወደ ተከፈተው አካውንት ማስገባታቸው፣ በደቡብ ሪጅን የግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮውን አንዳንዴ በገቢዎች በተከፈተው አካውት ገቢ ሲያደረጉ አንዳንዴ ደግሞ በሪጅን ጽ/ቤት በተከፈተ አካውንት ገቢ መደረጉን፣

92. በአዲስ አበባ ባሉ ውክልና የተሰጣቸው የገቢ ጽ/ቤቶች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ውስጥ በየወሩ ገቢ የማይሆኑ ሂሳቦች እንዳሉና በአመቱም መጨረሻ ብዙ ሂሳቦች ወደ ቀጣይ አመት እንዲዞሩ መሆናቸው፣

93. የገንዘብ ትልፍልፍን አስመልክቶ በኤጀንሲው በ29/08/05 ለባንክ የተላለፈ መመሪያ በወሩ መጀመሪያ እስከ 15ኛው ቀን የተሰበሰበውን በ16ኛው ቀን እና ከ16-30ኛው ቀን የተሰበሰበው በሚቀጥለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንድ መቶ ብር ብቻ በባንኩ ቀሪ ሆኖ ወደ ኤጀንሲው የባንክ ሂሣብ ቁጥር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲተላለፍ ለባንኮች መመሪያ ቢወርድም እየተተገበረ እንዳልሆነና ወደ ብሔራዊ ባንክ ተላልፈው ነገር ግን ብሔራዊ ባንክ ሳይገቡ እስከ 8 ወር፣ እንዲሁም ከገቢዎችም ሆነ ከንግድ ባንክ እስከ 1 አመት ሳይተላለፉ የሚቆዩ ሂሳቦች መኖራቸው ተገኝቶ ነበር፡፡

94. ኤጀንሲው ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በውል መሠረት ገቢውን እንዲሰበስቡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር /የጡረታ መዋጮው መሰብሰቢያ ሶፍትዌር እንዲኖራቸው በማድረግ እንዲሰበስቡ ሊያደርግና በትክክል በየወሩ ገቢ ስለመሆናቸው ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋና ከመንግሥትና ማህበራዊ ዋስትና ጋር ያለውን የአካውንት መደበላለቅ ችግር በመነጋገር በጋራ ሊፈታ እና ፣የገንዘብ ትልልፉን አስመልክቶ ከባንኮች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር በየጊዜው በመነጋገርና በመከታተል ሊቆጣጠር እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

95. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፊ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ከገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱ ጋር በጋራ መድረክ በመፍጠር በውሉ አፈፃፀም ላይ የታዩ ክፍተቶችን በተከታታይ በመገምገም እስከ ሰኔ 30, 2007 ዓ.ም የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ መግባባት ላይ እንደተደረሰ ፣ የተሰበሰቡ የተላለፉና ብሄራዊ ባንክ የገቡ ገንዘቦች አጣርቶ በየሳምንቱ ሪፖርት እንደሚቀርብ ፣ በተከታታይ እንደሚፈጸም ገልጿል፡፡

96. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

97. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታን መዋጮ ገቢን ለመሰብሰብ በኤጀንሲው የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የጡረታ መዋጮ ገቢ ከተደረገበት ልዩ ባንክ ሂሳብ በወቅቱ ለጡረታ ፈንድ ሂሳብ በትክክል ገቢ እንደሚያደርጉ እና ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች ከግል ድርጅቶች የሚሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ በትክክል ገቢ ስለማድረጋቸው የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት ገቢዎች ወደ ንግድ ባንክ ያስተላለፈበትን ባንክ ዲፖዚት ስሊፕ እና ባንክ ስቴትመንት በማምጣት እና የማስታረቅ ስራ በመስራት ቢሆንም ግን ያለው ስርዓት ደካማ እንደሆነ፣

98. የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ጋር በተደረገው የውል ስምምነት መሠረት ውሉን እየፈጸሙ ስለመሆናቸው ክትትል የሚደረገውም የቅ/ፅ/ቤቱን ሠራተኞች ገቢዎች ባለስልጣን በማስቀመጥ እንደሆነ እና በአሁኑ ወቅት ያለው አሰራር ከማክሰኞ እስከ ቅዳሜ የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ሰኞ ገቢ እንደሚደረግ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ቢገለፅም ከግል ድርጅቶች በገቢዎች ባለስልጣን የሚሰበሰበው ገንዘብ በትክክል የማይተላለፍ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

99. በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታን መዋጮ ገቢን ለመሰብሰብ በኤጀንሲው የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የጡረታ መዋጮ ገቢ ከተደረገበት ልዩ ባንክ ሂሳብ በወር አንድ ጊዜ ፣ ከንግድ ባንክ በሳምንት አንድ ጊዜ ወደ ብሄራዊ ባንክ ለጡረታ ፈንድ ሂሳብ ገቢ እንደሚደረግ እና ውክልና የሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች ከግል ድርጅቶች የሚሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ በትክክል ገቢ ስለማድረጋቸው የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት በወር አንድ ጊዜ ከንግድ ባንክ የባንክ አድቫይስ እና የባንክ መግለጫ በማምጣት እንዲሁም ሂሳቡን በማስታረቅ የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱን ሰራተኞች ገቢዎች ባለስልጣን በማስቀመጥ ቢሆንም የጡረታ መዋጮ እንዲሰበስቡ ውክልና የተሰጣቸው ገቢዎች ሲሆን ገቢዎች ላይ ክፍተት ያለ መሆኑን፣

100. ገቢዎች ባለስልጣን የባለቤትነት ስሜት ስለማይሰማቸው የጡረታ መዋጮውን በአግባቡ እየሰበሰቡ አለመሆኑን እና ከገቢ ሰብሳቢዎች የሚሰበሰበውን ገንዘብ ትልፍልፍን በተመለከተ ለንግድ ባንክ በሳምንት አንድ ጊዜ ወደ ብሄራዊ ባንክ

እንዲያስተላልፍ እንደሚደረግ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ቢገልፁም ከግል ድርጅቶች በገቢዎች ባለስልጣን የሚሰበሰበው ገንዘብ በትክክል የማይተላለፍ መሆኑን፣

101. በየካቲት ወር 2009 ዓ.ም ከልደታ ክፍለ ከተማ ገቢዎች የተሰበሰበው ብር መጠን 727,160.41 / ሰባት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አንድ መቶ ስልሳ ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም/ ሲሆን የተላለፈው የገንዘብ መጠን 262,609.41 / ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ዘጠኝ ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም/ መሆኑን፣ ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ ገቢዎች የተሰበሰበው ብር መጠን 4,689,350.07 / አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ ሶስት መቶ ሃምሳ ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም/ ሲሆን የተላለፈው የገንዘብ መጠን 864,019.38 / ስምንት መቶ ስልሳ አራት ሺ አስራ ዘጠኝ ብር ከ ሰላሳ ስምንት ሳንቲም መሆኑን፣

102. በ2008 ዓ.ም በገቢዎች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ብር መጠን 6,341,572.85 / ስድስት ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ አንድ ሺ አምስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሰማንያ አምስት ሳንቲም/ ሲሆን ወደ ባንክ የተላለፈው 5,615,096.39 / አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራአምስት ሺ ዘጠና ስድስት ብር ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም/ ፣

103. ከሀምሌ 2007 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 2009 ዓ.ም ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ብር 50,084,665.83 / ሀምሳ ሚሊዮን ሰማንያ አራት ሺ ስድስት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከሰማንያ ሶስት ሳንቲም/ ሲሆን ወደ ብሄራዊ ባንክ የተላለፈው የገንዘብ መጠን 49,302,218.21 / አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሁለት ሺ ሁለት መቶ አስራ ስምንት ብር ከ ሃያ አንድ ሳንቲም/ ሲሆን በዚሁ መሰረት ከተሰበሰበው የተላለፈው ሲቀነስ (50,084,665.83 - 49,302,218.21) = 782,447.62 / ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺ አራት መቶ አርባ ሰባት ከስልሳ ሁለት ሳንቲም/ ብር ሲሆን በባንክ ያለ ቀሪ ብር 90,563.68 / ዘጠና ሺ አምስት መቶ ስልሳ ሶስት ከ ስልሳ ስምንት ሳንቲም/ መሆኑን፣

104. ከ 782,447.62 ላይ 90,563.68 ባንክ ያለ ገንዘብ ሲቀነስ 691,883.94 / ስድስት መቶ ዘጠና አንድ ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ ሶስት ብር ከዘጠና አራት ሳንቲም/ ከገቢዎች ያልተላለፈ ገንዘብ መኖሩን፣

105. ከሀምሌ 2007 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 2009 ዓ.ም ከልደታ ክፍለ ከተማ የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ብር 9,689,805.18 / ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ

ሺ ስምንት መቶ አምስት ብር ከ አስራ ስምንት ሳንቲም/ ሲሆን ወደ ብሄራዊ ባንክ የተላለፈው የገንዘብ መጠን 8,553,813.34 / ስምንት ሚሊዮን አምስት መቶ ሃምሳ ሶስት ሺ ስምንት መቶ አስራ ሶስት ብር ከሰላሳ አራት ሳንቲም/ መሆኑን፣

106. በዚሁ መሰረት ከተሰበሰበው የተላለፈው ሲቀነስ (9,689,805.18-8,553,813.34)= 1,135,991.84 / አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ አምስት ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አንድ ብር ከ ሰማንያ አራት ሳንቲም/ ብር ሲሆን በባንክ ያለ ቀሪ ብር 359,690.27 /ሶስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺ ስድስት መቶ ዘጠና ብር ከሃያ ሰባት ሳንቲም/ መሆኑን እና ከ 1,135,991.84 ላይ 359,690.27 ባንክ ያለ ገንዘብ ሲቀነስ 776,301.57 / ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺ ሶስት መቶ አንድ ብር ከሀምሳ ሰባት ሳንቲም/ ከገቢዎች ያልተላለፈ ገንዘብ መኖሩን፣

107. በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ከገቢ ሰብሳቢዎች የሚሰበሰበውን ገንዘብ ወደ ኤጀንሲው የባንክ ሂሣብ ቁጥር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወቅቱ እና ሙሉ በሙሉ የማይተላለፍ መሆኑን ከኤጀንሲው የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እና ከባንክ መግለጫ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

108. በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ገቢዎች ባለስልጣን የሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ አንዳንድ ጊዜ ወደ ብሄራዊ ባንክ ገቢ እንደሚያደርጉ እና በትክክል ገቢ ስለማድረጋቸው የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት በወር አንድ ጊዜ ከንግድ ባንክ የባነክ መግለጫ በማምጣት እና ሂሳቡን በማስታረቅ መሆኑን፣

109. የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ጋር በተደረገው የውል ስምምነት መሠረት ውሉን እየፈጸሙ ስለመሆናቸው ገቢዎች ባለስልጣን ላይ ክትትል የሚደረገው የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱን ሰራተኞች ገቢዎች ባለስልጣን በማስቀመጥ እንደሆነ፣

110. ነገር ግን ገቢዎች ባለስልጣን ላይ አዳዲስ ሠራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች በሚቀየሩበት ጊዜ የጡረታ መዋጮውን እንደራሳቸው ገቢ የማይሰበስቡ ሲሆን ከገቢ ሰብሳቢዎች የሚሰበሰበውን ገንዘብ በየሳምንቱ ወደ ብሄራዊ ባንክ እየተላለፈ እንደሚገኝ፣ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ ቢሆንም ከግል ድርጅቶች በገቢዎች የሚሰበሰበው ገንዘብ መጠን በትክክል የማይተላለፍ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ከባንክ መግለጫ /Bank Statement/ መረጃ ለማወቅ ችሏል፡፡

111. በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት ገቢን ለመሰብሰብ በኤጀንሲው ውክልና የሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ የማይሰበስቡላቸው እንደሆነ፣ የግል ድርጅቶች እራሳቸው በኤጀንሲው የንግድ ባንክ የሂሳብ ቁጥር ቀጥታ ገቢ የሚያደርጉ ሲሆን ከግል ድርጅቶች የሚሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ በትክክል በየወሩ ገቢ ስለማድረጋቸው የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት ከባንክ የባንክ አድቫይስ እና የባንክ መግለጫ በማምጣት መሆኑን፣

112. የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ጋር በተደረገው የውል ስምምነት መሠረት ውሉን እየፈጸሙ ስለመሆናቸው ክትትል እንደሚያደርግ፣ ክትትል የሚያደርገውም ወር ሁለት ጊዜ ወደ ገቢዎች ባለስልጣን በመሄድ እና የግል ድርጅቶች ለገቢዎች ባለስልጣን የጡረታ መዋጮ ገቢ ያደረጉበት የባንክ መረጃዎችን በማምጣት ሲሆን አበል ከፋይ ተቋማት ላይ ደግሞ ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ መተማመኛ በመፈራረም ያልተከፈለ ካለ በመተማመኛው መሰረት ቁጥጥር እንደሚደረግ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

113. የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡትምላሽ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት የጡረታን መዋጮ ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ የግል ድርጅቶች ወደ ጡረታ ፈንዱ አካውንት የጡረታ መዋጮውን እራሳቸው ገቢ የሚያደርጉ መሆኑን፣ ወደ ገቢዎች የሚወስዱት ገቢ ያደረጉበትን ማስረጃ/ ዲፖዚት ስሊፕ/ ሲሆን የጡረታ መዋጮ በትክክል በየወሩ ገቢ ስለማድረጋቸው የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት ከባንክ የባንክ አድቫይስ እና የባንክ መግለጫ በማምጣት መሆኑን፣

114. የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ጋር በተደረገው የውል ስምምነት መሠረት ውሉን እየፈጸሙ ስለመሆናቸው ክትትል እና እንደሚደረግ እና ከባንክ በወር ሁለት ጊዜ የባንክ አድቫይስ በማምጣት በሪፖርት ለኤጀንሲው የሚየሳውቁ መሆኑን፣ አንዳንድ ጊዜ የገንዘብ ትልልፉ በተባለው ቀን ወደ ብሄራዊ ባንክ እንደማይገባ ታውቋል፡፡

115. የሀዋሳ ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን የጡረታ መዋጮ ኤጀንሲውን ወክለው እንደማይሰበስቡ ከሀዋሳ ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

116. በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታን መዋጮ ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ የግል ድርጅቶች ወደ ጡረታ ፈንዱ አካውንት የጡረታ መዋጮውን እራሳቸው ገቢ

የሚያደርጉ መሆኑን፣ ወደ ገቢዎች የሚወስዱት ገቢ ያደረጉበትን ማስረጃ/ ዲፖዚት ስሊፕ/ እንደሆነ፣ የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ላይ በሚፈለገው ልክ እና ወጥነት ባይኖረውም ውሉን እየፈጸሙ ስለመሆናቸው ክትትል እና ቁጥጥር እንደሚደረግ እና ከደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፣

117. ንግድ ባንክ የገባው የጡረታ መዋጮ በየ 15 ቀኑ ወደ ብሄራዊ ባንክ እየተላለፈ መሆኑን እና በትክክል ስለመተላለፉ የባንክ መግለጫ በማምጣት የሚያረጋግጡ መሆኑን የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ቢገልፁም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወደ ብሄራዊ ባንክ ያለው የገንዘብ ትልልፍ በወቅቱ እና በአካውንቱ ሙሉ ለሙሉ እንደማይተላለፍ ከባንክ መግለጫ /Bank statmenet/ ለማወቅ ተችሏል፡

118. በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት የጡረታን መዋጮ ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ የግል ድርጅቶች ወደ ጡረታ ፈንዱ አካውንት የጡረታ መዋጮውን እራሳቸው ገቢ የሚያደርጉ መሆኑን እና ይህን በተመለከተ ከገቢዎች ባለስልጣን ጋር የሚሰሩት ስራ አለመኖሩን፣

119. የጡረታ መዋጮ በትክክል ገቢ ስለመደረጉ የሚያረጋግጡት የባንክ መግለጫ በማምጣት እና ሂሳቡን በማስታረቅ እንደሆነ እና የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ላይ ውሉን እየፈጸሙ ስለመሆናቸው ክትትል እና ቁጥጥር እንደሚያደርጉ ንግድ ባንክ የገባው የጡረታ መዋጮ በየ 15 ቀኑ ወደ ብሄራዊ ባንክ እየተላለፈ መሆኑን እና በትክክል ስለመተላለፉ የባንክ መግለጫ በማምጣት የሚያረጋግጡ እንደሆነ የሚመለከተጨው የሥራ ሃላፊዎች ቢገልፁም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወደ ብሄራዊ ባንክ ያለው የገንዘብ ትልልፍ በወቅቱ እና በአካውንቱ ሙሉ ለሙሉ እንደማይተላለፍ ከባንክ መግለጫ /Bank statmenet/ ለማወቅ ተችሏል፡፡

120. በኤጀንሲው እስከ ሚያዝያ 30,2009 ወደ ብ/ባንክ ተላልፈዋል ተብለው እስከ ጥቅምት 09፣2009 ድረስ የኤጀንሲው ብሄራዊ ባንክ አካውንት ገቢ ያልሆኑ ገንዘቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- በደቡብ ሪጅን የሚያዚያ ወር 7,050.42 ብር፣
- በመርካቶ 1 የመጋቢት 446,976.06 ብር፣
- በአቃቂ የመጋቢት ወር ብር 202,415.86

- በልደታ የመጋቢት ወር 15,967.7 ብር
- በቂርቆስ የመጋቢት ወር 1,896.00 ብር
- በቦሌ የጥር ወር 188,284.00 ብር ሲሆን

121. በጠቅላለው 862,590.04 ወደ ብሄራዊ ባንክ ተላልፈው ወደ ኤጀንሲው አካውንት ገቢ ያልሆኑ መሆንቸውን እንዱሁም በወር አራት ጊዜ ገንዘብ ወደ ብሄራዊ ባንክ ማስተላለፍ ሲገባቸው በጥር ወር 2009 ዓ.ም መርካቶ1፣ አራዳ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ ልደታ፣ እና መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር2 ከ አራት ጊዜ በታች ማስተላለፋቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

122. በተጨማሪም በኤጀንሲው በ2009 በጀት ዓመት (ከሀምሌ 2008 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 2009 ዓ.ም ወደ ብሄራዊ ባንክ በተላለፈው ሪፖርት ውስጥ ሳይጠቀስ ብሄራዊ ባንክ ገብተው የተገኙ የማን እንደሆኑ ሳይታወቁ ወደ ብሄራዊ ባንክ የገቡ ገንዘቦች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዝርዝሩ ከታች በሠንጠረዥ ተቀምጧል፡፡

የተላለፈበት ንግድ ባንክ/ገቢ ሰብሳቢ	የገንዘብ መጠን	ብ/ባንክ የገባበት ቀን
ሀርር	4,132,657.57	22/2/20017
››	2,702,098.62	3/3/2017
››	996,710.68	3/3/2007
ቦረና ዞን	504,270.56	3/3/2017
››	153,000.00	11/2/20017
ጭሮ ከተማ	39,353.4	28/2/2017
አዶላ	20,607.46	10/2/2017
››	7,970.17	3/3/2017
አቃቂ	3,420.00	25/10/2016
ጠመንጃ ያዥ	2,400	11/7/2016
››	1,506.00	20/2/2017
››	1,347,135.79	6/4/2017
አዲስ ከተማ	390,365..37	4/4/2017
ኮልፌ	166,024.09	21/3/2017
››	144,079.80	13/2/2017
››	3,002,173.89	8/5/2017
››	2,292,630.00	13/4/2017
››	2,260,934.00	13/42017
ጭሮ ቅርንጫፍ	62,205.13	28/2/2017
ቂርቆስ	338,904.45	4/5/2017
››	112,566.67	8/5/2017
ደ/ምዕራብ	18,307.88	10/4/2017

123. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ተሰብስበው ወደ ብሄራዊ ባንክ በወቅቱ የማይተላለፍ ሂሳቦች ቀደም ሲል በስፋት የሚታዩ ቢሆንም አሁን ባለው ሁኔታ ችግሩ በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱን፣ በየአስራአምስት ቀናት ተሰብስቦ ወደ ብሄራዊ ባንክ የተላለፍና ይቀረ ሂሳብ ለበላይ አመራሩ ሪፖርት እንደሚቀርብ እና ክፍተቶች ሲታዩ ከባንኮች ጋር በመነጋገር ለማስተካከል ጥረት እንደሚደረግ፣

124. የማይታወቁ ሂሳቦችን በተመለከተ በባንኮች በኩል የሚፈጠር ስህተት ወደ ኤጀንሲው አካውንት ገብቶ የሚታይበት ሁኔታ የሚያጋጥም መሆኑን፣ የኤጀንሲው ያልሆኑት ሂሳቦች ተረጋግጠው እንዲቀርቡ ሲጠየቅ ለማጣራትና የማን ሂሳብ እንደሆነ ለመግለጽ በባንኮች በኩል ረዘም ያለ ጊዜ እንደሚወስድ እና ተጣርቶ በሚታወቅበትና ባለቤቱ ሂሳቡ ይመለስልኝ ብሎ በሚጠይቅበት ጊዜ ወዲያዉኑ ተመላሽ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

ኤጀንሲው ግዴታቸውን በማይወጡ የግል ድርጅቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ <u>የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋና ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡</u>

125. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

126. ይሁንና በዋናው መ/ቤት፣ በሪጅንና ቅ/ጽ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የሂሳብ መዝገብ በማይዙ፣ መረጃ በማይሰጡ እና በወቅቱ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ ተለይቶ የተቀመጠ መረጃ የሌለ መሆኑን፣ ግዴታቸውን በማይወጡ የግል ድርጅቶች ላይ እርምጃ እተወሰደ አለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

127. ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የሂሳብ መዝገብ በማይዙ እና መረጃ በማይሰጡ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ መረጃዎችን በመለየት በወቅቱ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

128. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፈ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በቋሚነትና በተከታታይ እንደሚፈጸም ገልጿል፡፡

129. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

130. የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ፡-

131. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት በግል ድርጅቶች የሒሳብ መዝገብ ይኑር ወይም አይኑር እንደማያውቁ፣ መረጃ በማይሰጡና በወቅቱ የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ እንደሚወስዱ እና ህጋዊ እርምጃም የሚወስዱትም ገቢዎች ባስቀመጧቸው የቅ/ፅ/ቤቱ ሠራተኞች ክትትል በማድረግ እንደሆነ፣

132. በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የሂሳብ መዝገብ በማይዙ ፣ መረጃ በማይሰጡ እና በወቅቱ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ስርአትን በተመለከተ የመረጃ አያያዝ ክፍተት መኖሩን፣ አሁን የአጠቃላይ የድርጅቶች መረጃ በማደራጀት ወደ መረጃ ቋት በማስገባት ላይ መሆናቸውን እና ችግሩ የተፈጠረው ስራው ሲጀመር መረጃ እየተያዘ ስላልተጀመረ እንደሆነ፣

133. በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የሂሳብ መዝገብ በማይዙ ፣ መረጃ በማይሰጡ እና በወቅቱ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ስርአት ሌጀር እንደሆነ እና በሌጀር እንደሚቆጣጠሩ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ቢገልፁም ሌጀሩ የተሟላ አለመሆኑን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት መቻሉ፣

134. በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት ፣ በደቡብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት እና በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የሂሳብ መዝገብ በማይዙ ፣ መረጃ በማይሰጡ እና በወቅቱ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ስርአት የተዘረጋ መሆኑን የሚመለከተቸው የስራ ሃላፊዎች ቢገልፁም የተዘረጋ የመረጃ አያያዝ ስርዓት አለመኖሩን የኦዲት ቡድኑ መመልከቱን፣

135. በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ ፣ የሂሳብ መዝገብ በማይዙ ፣ መረጃ በማይሰጡ እና በወቅቱ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ስርአት ክፍተት መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

136. በባህር ዳር ሰሜን ምዕራብ ሪጅን /ፅ/ቤት ለሳትኮን ኮንስትራክሽን ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ሪፈራል ሆስፒታል ፕሮጀክት ከታህስስ 2007 ዓ.ም ጀምሮ የጡረታ መዋጮ ገቢ ያደረጉበትን መረጃ አለማቅረቡን፣ እንዲሁም የባንክ ሂሳብ ቁጥር ያላሳወቀ አለማሳወቁን ኤጀንሲው ከፃፋቸው ደብዳቤዎች ለማወቅ ተችሏል።

137. በባህር ዳር ሰሜን ምዕራብ ሪጅን /ፅ/ቤት መራዓዊ ከተማ የሚገኘው ኢትዮጵያ ሆቴል ፣ ማራኪ ካፌና ሪስቶራንት ፣ ክብረቱ መለስተኛ ክሊኒክ፣ ቢራራ ጠቅላላ ብረታ ብረት ስራ ድርጅት፣ ቄስ ፍሬው ዘሪሁን ልዩ ልዩ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ድርጅቱ፣ ሃይለ ስላሴ መካከለኛ ክሊኒክ፣ የሻለም ዳቦ መጋገሪያና ማካፋፈያ ድርጅት፣ የዉቢት ሆቴል ፣ እሮቢት ሆቴል ፣ ለንደን ሆቴል ፣ ቆጋ ባርና ሬስቱራንት ፣ ሙስጠፋ ነዳጅ ማደያ ፣ ሲስተር ንግስት መለስተኛ ክሊኒክ፣ ፒታ ካፌና ሬስቶራንት፣ ካቶሊክ ዳሽን ባንክ በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችን ባለማስመዝገብ እና የሰራተኛውን ደመወዝ መነሻ በማድርግ የጡረታ መዋጮ የተቀነሰበትን ማስረጃ ሊያቀርቡ ፈቃደኝ ሊሆኑ አለመቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

138. እንዲሁም በባህር ዳር ከተማ በባህር ዳር ከተማ ኮማንደር ብርሃኑ ገ/ፃድቅ/ የደጀን የጥበቃ ጠሰው ሃይል አገለግሎት ስራ አስኪያጅ፣ የደጀን የጥበቃና የሰው ሃይል አገለግሎት ኃ/የተ/የግል ማህበር ፣ ሳምሶን ኮንስትራክሽን እና ጣና ስራ ተቋራጭ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችን በማስመዝገብ ሰራተኞችን የጡረታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በተደጋጋሚ ተነግሯቸው ማሰጠንቀቂ ቢሰጥም ፈቃደኛ ባለመሆን አዋጁ የጣለውን ግዴታ ሊወጡ አለመቻላቸውን ፣ በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችን ባለማስመዝገብ እና የሰራተኛውን ደመወዝ መነሻ በማድርግ የጡረታ መዋጮ የተቀነሰበትን ማስረጃ ሊያቀርቡ ፈቃደኝ ሊሆኑ አለመቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

139. ደቡብ ሪጅን ጽ/ቤት በሀዋሳ ከተማ የሚገኘው አልማታ ኢ/ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ የድርጅትና የሠራተኞች ምዝገባ እንድያከናውን የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ጥቅምት 08 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠው ቢሆንም ምዝገባ ያለከናወነ መሆኑን፣ ከሐምሌ 2003ዓ.ም- ታህሳስ 2007 ዓ.ም ያለዉን ፔሮልና የባንክ ስሊፕ ያላቀርቡ መሆኑን፣

140. ሀዋሳ ገነት ሆቴል የጡረታ መዋጮ ገቢ ምረመራ ለማደረግ የሆኑ ሰነዶችን የስራ ግብር እና ጡረታ የተከፈለበት ፔሮል እና ደረሰኝ፤ ከ60 ዓመት በላይ የሆኑ ጡረታ የማይከፍሉ ሠራተኞች ካሉ ዕድሜያቸውን የሚገልጽማስረጃ፤ሁለት እና ከዚያ ቦታ የሚሰሩ ሰራተኞች ካሉ ጡረታ ለመቀጠል የወሰነበት ድርጅት፤የድርጅታቸውን የባንክ

ሂሳብ ቁጥርና ሙሉ አድራሻ፤የውጭ ዜጎች ካሉ ዜግነታቸውን የሚገልጽ መረጃ፤ እና ከ ሰራተኞች ቅጥር ጀምሮ እስከ የካቲት 30,2009 ዓ.ም ድረስ ያሉ ደረሰኞች ኮፒ ያላቀረቡ መሆኑን፣

ኤጀንሲው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን በመሰብሰብና የሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ የጡረታ መዋጮ ገቢ ማቀዱንና አጠቃላይ የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ መዘጋጀቱን በተመለከተ፤

141. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

142. በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ በጎንደር፣ በደብረማርቆስና በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት የጡረታ መዋጮ ዕቅዳቸው በአካባቢያቸው ያሉትን የግል ድርጅት ሠራተኞች የደመወዝ መረጃ በመሰብሰብ ሳይሆን እስካሁን በግምት ከዋናው መ/ቤት እንደሚወርድና ከዋናው መ/ቤት በተሰጣቸው ለመሥራት ከመሄድ ውጭ በክልላቸው የተለየ መረጃ እንደሌላቸው እንዲሁም በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት የጡረታ መዋጮ ገቢ ሲታቀድ በተመሳሳይ በግምት እንደሆነና መነሻ እንደሌለው በአካባቢያቸው ትልልቅ የግል ድርጅቶች ያሏቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም ሆኑ ትንንሽ የግል ድርጅቶች ያሉባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እኩል እንዲሰበስቡ ተደርጎ እንደሚታቀድ፣

143. በሰሜን ምዕራብ ሪጅን መዋጮም ላይ የመነሻ ጥናት እንደሌለና በየአመቱ ፐርሰንቱ ስለሚጨምር ይጨምራል በሚል መነሻ እንደሆነና ያለፈው አመት አፈፃፀም በማየት እንደሚከፋፈሉ የገለጹ መሆኑን፣

144. ከኤጀንሲው ዕቅድ አፈጻጸምና ከሥራ አመራር ቃለ ጉባኤ በተገኘ መረጃ እስካሁን የኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ዕቅድ አፈፃፀም በ3 አመት ውስጥ ከ100 ፐርሰንት በላይ የሆነና የማይከፍሉና ያልተመዘገቡ በርካታ የግል ድርጅቶች ባሉበት አፈፃፀሙ ይህን ያህል መድረሱ መነሻ ባለመኖሩ ዕቅዱ ሲታቀድ ከአቅም በታች መታቀዱን የኦዲት ቡድኑ ለመረዳት የቻለ ሲሆን የኤጀንሲውን አጠቃላይ የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ በኤጀንሲው ስለመዘጋጀቱም በኦዲቱ ወቅት መረጃ አለመቅረቡ ተገኝቶ ነበር፡፡

145. ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ገቢን ሲያቅድ በተጨባጭ በከተሞችንና በሪጅን ደረጃ ያሉ የግል-ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን በመሰብሰብና ጥናት በመጥናትና ጥናቱን መሠረት በማድረግ ሊያቅድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

146. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፈ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር የጡረታ መዋጮ ገቢ ዕቅድ ማዘጋጀት እስከ ሰኔ 30, 2007 እንደሚጠናቀቅ፣ እና የጡረታ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ በየበጀት አመቱ መጨረሻ እንደሚዘጋጅ ገልጿል፡፡

147. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

148. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በቀጣይ አመት መሰብሰብ ያለበትን የጡረታ መዋጮ ገቢ የማያቅድ መሆኑን፣ እቅዱ ከላይ ወደታች የሚወርደው እንደሆነ እና በቅርጫፍ ፅ/ቤት ደረጃ የሚያቅዱት ነገር አለመኖሩን፣

149. በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው እቅድ የሚያቅደው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በቀጣይ አመት መሰብሰብ ያለበትን የጡረታ መዋጮ ገቢ አቅዶ ሳይሆን ባለፈው ዓመት ከተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ በመነሳት እና የሚጨመሩ የግል ድርጅቶችን እና ሰራተኞችን ግምት መሰረት በማድረግ መሆኑን፣

150. በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ እቅድ የሚመጣው ከዋናው መ/ቤት ሲሆን ለቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ የሚመጣው ከሪጅን ፅ/ቤት መሆኑን እና የሚታቀደው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን በመሰብሰብና የሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በቀጣይ አመት መሰብሰብ ያለበትን የጡረታ መዋጮ ገቢ አቅዶ ሳይሆን ከእስትራቴጂክ እቅዱ በየዓመቱ በማከፋፈል መሆኑን፣

151. በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው የሚያቅደው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ሳይሆን ኤጀንሲው ለደቡብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት አቅዶ ይልካል፣ ሪጅኑ ደግሞ ለቅርንጫፍ ፅ/ቤታቸው የሚልክ እንደሆነ፣

152. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ኤጀንሲው የሚያቅደው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ሳይሆን የተመዘገቡ ፣ አዲስ የሚመዘገቡ እና የሚዘጉ ድርጅቶችን ታሳቢ በማድረግና ያለፈውን ዓመት አፈፃፀም በማየት እንደሆነ፣

153. በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው የሚያቅደው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ሳይሆን የእቅዳቸው መነሻ ያለፈው ዓመት የእቅድ አፈፃፀም መሆኑን፣

154. በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው የሚያቅደው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ሳይሆን የእስትራቴጂክ እቅዱን እና ያለፈውን ዓመት እቅድ አፈፃፀም መሰረት በማድረግ እንደሆነ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ታውቋል፡፡

155. ኤጀንሲው የተሰብሳቢና የተከፋይ ሰነዶችን፣ ከኢንቨስትመንት የተገኘ ገቢ (ትርፍ) እና የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴን በመከታተል የኤጀንሲውን አጠቃላይ የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ ማዘጋጀቱን እና መግለጫ ማቅረቡን በተመለከተ የኤጀንሲው ፈንድና ኢንቨስትመንት ዳይሬክቶሬት የሥራ ሃላፊ ኤጀንሲው የተሰብሳቢና የተከፋይ ሰነዶችን፣ ከኢንቨስትመንት የተገኘ ገቢ (ትርፍ) እና የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴን በመከታተል የኤጀንሲውን አጠቃላይ የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ የሚዘጋጅ መሆኑን እና በውጪ ኦዲተርም እንደሚመረመር ገልፀዋል፡፡፡

ኤጀንሲው ትርፋማነታቸው በተረጋገጠ ኢንቨስትመንቶች ላይ በመሰማራት ፈንዱን <u>ማዳበሩን በተመለከተ፤</u>

156. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

157. ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ የግል ድርጅቶቹ በወቅቱ እንዲከፍሉ የሚያስችል አስገዳጅ ህግ ባለመውጣቱና በማይመዘገቡና በማይከፍሉ ድርጅቶች ላይ በወቅቱ እርምጃ ባለመውሰዱ የጡረታ መዋጮውን በወቅቱ አሟጦ የማይሰበስብ መሆኑን ለማወቅ የተቻለና ገቢውም በወቅቱ ተሰብስቦ ወደ ብሔራዊ ባንክ ባለመግባቱ ትሬዠሪ ላይ ውሎ ማግኘት የሚገባውን ትርፍ ማግኘት አለመቻሉ ፣

158. በተጨማሪም የጡረታ አዋጁ አንቀጽ 13 ቁጥር 1/ለ/ ላይ የጡረታ ፈንዱ ለትሬዠሪ ቦንድ መግዣና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ

ለሚወሰኑ ሌሎች አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች ያውላል ቢልም እየዋለ ያለው በትሬዠሪ ቦንድ ሽያጭ ላይ ብቻ በመሆኑ ኤጀንሲው በተጨማሪ ማግኘት ያለበትን ትርፍ እንዳያገኝና የጡረታ ፈንዱን አሁን ካለው በተጨማሪ ሊዳብር አለመቻሉ ተገኝቶ ነበር፡፡

159. ኤጀንሲው የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ አሟጦ ሊሰበስብና የጡረታ መዋጮ ገቢ ፈንድን ትርፋማነታቸው በተረጋገጠ ዘላቂና አስተማማኝ በሆኑ የሥራ መስኮች ላይ ለመሰማራት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴ መመሪያ ሊወጣና ሊተገበር እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

160. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፈ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ኤጀንሲው ትርፋማነታቸው በተረጋገጠ ኢንቨስትመንቶች ላይ በመሰማራት ፈንዱን ማዳበሩን በተመለከተ አላካተተም

161. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

162. ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቃለ- መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው፡-

163. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ አሟጦ እንደማይሰበስብ ፣ ለዚህም ምክንያቱ የተሟላ ነገር የሌለ መሆኑን፣ የኦዲት ባለሞያዎች የግል ድርጅቶች ላይ እየዞሩ ኦዲት ለማድረግ የተዘጋጀ ተሽከርካሪ ወይም የትራንስፖርት ክፍያ ባለመኖሩ ኦዲት እያደረጉ ያሉት በእግራቸው በመሄድ እንደሆነ እና በቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ምንም ዓይነት ተሽከርካሪ ባለመኖሩ ስራ መስራት አለመቻሉን፣

164. በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ተሟጦ ተሰብስቧል ለማለት እንደማይቻል፣

165. በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ተሟጦ የማይሰበሰብ መሆኑን፣

166. በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ አሟጦ ይሰበሰባል ለማለት እንደማይቻል እና ድርጅታቸውንና ሰራተኞቻቸውን አስመዝግበው የጡረታ መዋጮ የማይከፍሉ የግል ድርጅቶች መኖራቸውን፣

167. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ አሟጠው እንደማይሰበሰብ፣

168. በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት ፈንዱን ለማዳበር መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ አሟጦ ይሰበሰባል ለማለት እንደማይቻል፣

169. በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ የዓመቱን እቅድ ሙሉ ለሙሉ የሚፈፅሙ መሆኑን ነገር ግን መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ አሟጠው እንዳልሰበሰቡ ለማወቅ ተችሏል፡፡

170. ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ገቢ ፈንድን ትርፋማነታቸው በተረጋገጠ ዘላቂና አስተማማኝ በሆኑ የሥራ መስኮች ላይ በመሰማራት ፈንዱን ማዳበሩን በተመለከተ የኤጀንሲው ፈንድና ኢንቨስትመንት ዳይሬክቶሬት የሥራ ሃላፊ የጡረታ መዋጮ ገቢ ፈንድን ትርፋማነታቸው በተረጋገጠ ዘላቂና አስተማማኝ በሆኑ የሥራ መስኮች ላይ በመሰማራት ፈንዱን ማዳበርን በተመለከተ ለጊዜው በተፈቀደው የመንግስት የግምጃ ቤት ሰነድ ብቻ በመሆኑ በዚሁ መስክ ብቻ መዋዕለ ንዋያቸውን እንደሚያፈሱ ገልፀዋል፡፡

171. ነገር ግን ኤጀንሲው የመንግስት የግምጃ ቤት በመግዛት የሚያገኘው ትርፍ በ ዘጠና አንድ ቀን ውስጥ ከአንድ ብር 0.3 ሳንቲም ሲሆን ይህ ማለት አሁን ካለው የባንክ ወለድ ጋር እና ካለው የኑሮ ግሽበት ቢነፃፀር እንኳን የትርፍ መጠኑ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ያምናል፡፡

172. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የጡረታን መዋጮ በወቅቱ በመሰብሰብና በኢንቨስትመንት ላይ እንዲውል ለማድረግ ተገቢው ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን፣ ባልተከፈለ የጡረታ መዋጮ ላይም ወለድና ቅጣት በማከል እየተሰበሰበ እንደሚገኝ፣ የጡረታ መዋጮን አሟጦ በየወሩ በመሰብሰብ ውዝፍ እንዳይኖር ለማድረግ በቀጣይም ሥራው ተጠናክሮ በመቀጠል በቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆን ስላለበት በዚሁ አግባብ ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣

173. ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ቀደም ሲል በክዋኔ ኦዲት በተሰጠ ምላሽ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው በተለያዩ ኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ የጡረታ ፈንዱን ኢንቨስት በማድረግና የተሻለ ትርፍ ማግኘት ያልተቻለው በኤጀንሲው የአፈጻጸም ድክመት ሳይሆን ያለው የህግ ማዕቀፍ /አዋጅ/ ስለማይፈቅድና መፍትሄ ለማግኘት እስካሁን

የተደረገው ጥረት ባለመሳካቱ መሆኑን እና ጉዳዩ ለፈንዱ መጠናከርና ዘላቂነት ወሳኝ በመሆኑ በኤጀንሲው በኩል ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልፀዋል፡፡

ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ ፈፃሚ አካላትንና ባለድርሻ አካላትን ማሳተፉን፣ የተቋማቱን አቅም ለማጐልበት ስልጠና መስጠቱን እንዲሁም በኤጀንሲው የሚሰጡ አገልግሎቶችን <u>በመገምገም ግብረ መልስና ሙያዊ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፤</u>

174. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

175. በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ ሁሉም በናሙና በታዩ ሪጅንና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ባለድርሻ አካላት ዕቅድ ሲታቀድ ጽ/ቤቶቹን በማሳተፍና ከጽ/ቤቶቹ መረጃ እና አቅም በመነሳት ሳይሆን ምዝገባ ላይ ስትራቴጂክ ዕቅዱን ማሳካት አለብን በሚል ከዋናው መሥሪያ ቤት አመታዊ ዕቅድ እንደሚቀርብና በቀረበው ላይ እንደሚወያዩ ነገር ግን በውይይቱ ወቅት በሰጡት አስተያየት መሠረት ማስተካከያ እንደማይደረግና በተጨባጭ መረጃ ባለመኖሩ አቅም ያላገናዘበ፣ የተጋነነ ዕቅድ እንደተሰጣቸውና ሠራተኛ ምዝገባን ማሳካት እንዳልቻሉ፣

176. እንዲሁም ኤጀንሲው በሪጅንና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የሚሰጡ አገልግሎቶችን አፈፃፀም መገምገሙ፣ ግብረ መልስና ሙያዊ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ ወጥ በሆነ ምልኩ የክትትልና የድጋፍ ሥራ እየተሰራ አለመሆኑና ፣

177. ስልጠና አብዛኛውን ጊዜ የማይሰጥና አልፎ አልፎ ሲሰጥም በተደራጀ መልኩ ሞጁልና ማንዋልን መሠረት ያደረገ፣ ክፍተቶቻቸውን ተጠይቀው መሰረታዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት የሚያስችልና በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ ፣ ከሥራው ውስብስብነትና ሰፊ ከመሆኑ አንጻር ግንዛቤ ማስጨበጫ እንጂ ስልጠና ሊባል የማይችል እንደሆነና ለኃላፊዎችም የአመራር ስልጠናም እየተሰጠ አለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

178. ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ ሪጅንና ቅ/ጽ/ቤቶችን ሊያሳትፍ እንዲሁም ወጥ በሆነ መልኩ በእቅድ ይዞ ክትትል በማድረግና ክፍተቶችን በመለየት ግብረ መልስም ሆነ ድጋፍ ሊሰጥ እንደሚገባ ዕቅድ በመያዝ ወጥ በሆነ መልኩ የፈፃሚ አካላትን ሥራ ሊከታተልና በተገኙ ክፍተቶች ላይ ግብረ መልስ በመስጠት ሙያዊ ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ፣

179. በሪጅንና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ላሉ ሠራተኞች እንዲሁም ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ ተቋማትን ያለባቸውን ክፍተት በመለየትና የፍላጎት ጥናት በማድረግ በተደራጀ መልኩ ሞጁልና ማንዋልን መሠረት ያደረገ ስልጠና ሊሰጥና አዲስ ለሚቀጠሩ ሠራተኞችም የጡረታ ምዝገባ አሰባሰብ አዲስ እንደመሆኑ እንዲያው ስልጠና ሊሰጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

180. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፈ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በተከታታይ እንደሚሰራ ገልጿል፡፡

181. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

182. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ የሪጅን፣ የቅ/ጽ/ቤቶችንና ባለድርሻ አካላትን እንደማያሳትፍ፣ እንዲያውቁት የሚደረገው እቅዱ ከታቀደ በኋላ ሲሆን ከላይ ታቅዶ ወደ ቅ/ፅ/ቤታቸው የሚመጣው እቅድ ከእንርሱ አቅም ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ፣ ኤጀንሲው የተቋማቱን አቅም ለማጐልበት የፍላጎት ጥናት በማድረግ ለሰራተኞች ስልጠና የማይሰጥ መሆኑን፣ እና ኤጀንሲው በሪጅንና በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የሚከናወኑና የሚሰጡ አገልግሎቶችን አፈፃፀም ገምግሞ በተገኙ ክፍተቶች ላይ ግብረ መልስ እንደሚሰጥ ነገር ግን ሙያዊ ድጋፍ የማይደረግ መሆኑን፣

183. በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ ለአዲስ አበባ ሪጅን እንደሚያስተላልፍ፣ አዲስ አበባ ሪጅን ደግሞ በእቅዱ ላይ እንደሚያሳትፋቸው ፣ የተቋማቱን አቅም ለማጐልበት የፍላጎት ጥናት በማድረግ ለሰራተኞች ስልጠና እየተሰጠ አለመሆኑን፣ አዲስ የሚቀጠሩ ሰራተኞችም ስልጠና ሳይሰጣቸው ቀጥታ ወደ ስራ የሚገቡ እንደሚገቡ፣ እና ኤጀንሲው በሪጅንና በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የሚከናወኑና የሚሰጡ አገልግሎቶችን አፈፃፀም ገምግሞ በተገኙ ክፍተቶች ላይ ግብረ መልስ የሚሰጥ ቢሆንም ሙያዊ ድጋፍ እንደማያደርግ፣

184. በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ የማያሳትፋቸው ቢሆን ውይይት የሚያደርጉት እቅዱ ከታቀደ በኋላ እንደሆነ፣ የተቋማቱን አቅም ለማጐልበት የፍላጎት ጥናት በማድረግ ለሰራተኞች ስልጠና እየሰጠ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ ስልጠና እየተሰጠ አለመሆኑን፣ እና ኤጀንሲው በሪጅንና በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ

የሚከናወኑና የሚሰጡ አገልግሎቶችን አፈፃፀም ገምግሞ በተገኙ ክፍተቶች ላይ ግብረ መልስ እንደሚሰጥ ነገር ግን ሙያዊ ድጋፍ እንደማያደርግ፣

185. በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ የሪጅን፣ የቅ/ጽ/ቤቶችንና ባለድርሻ አካላትን የማያሳትፍ እንደሆነ፣ የተቋማቱን አቅም ለማጐልበት የፍላጎት ጥናት በማድረግ ለሰራተኞች ስልጠና እንደማይሰጥ እና ኤጀንሲው በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የሚከናወኑና የሚሰጡ አገልግሎቶችን አፈፃፀም ሊገመግምና በተገኙ ክፍተቶች ላይ ግብረ መልስና ሙያዊ ድጋፍ እንደሚሰጥ፣

186. የሆሳዕና እና የሀዋሳ ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን ኤጀንሲው በሚያቅደው እቅዶች ዙሪያ ለመወያየት አሳትፎዋቸው እንደማያውቅ ፣

187. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ የሚያሳትፋቸው ቢሆንም ተሳትፎው ሙሉ አለመሆኑን፣የተቋማቱን አቅም ለማጐልበት የፍላጎት ጥናት በማድረግ ለሰራተኞች ስልጠና እንደማይሰጥ ነገር ግን ደካማ አፈፃፀም ላላቸውን ሰራተኞች ስልጠና እንደሚሰጥ እናኤጀንሲው በሪጅንና በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የሚከናወኑና የሚሰጡ አገልግሎቶችን አፈፃፀም ቁጥጥር ተደርጎ በተገኙ ክፍተቶች ላይ ግብረ መልስ የሚሠጥ መሆኑን፣

188. በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ የሪጅን፣ የቅ/ጽ/ቤቶችንና ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ እነደሆነ፣ የተቋማቱን አቅም ለማጐልበት የፍላጎት ጥናት በማድረግ ለሰራተኞች ስልጠና እየተሰጠ አለመሆኑን ፣ እና ኤጀንሲው በሪጅንና በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የሚከናወኑና የሚሰጡ አገልግሎቶችን አፈፃፀም ገምግሞ በተገኙ ክፍተቶች ላይ ውይይት የሚደረግና ግብረ መልስ የሚሰጥ ቢሆንም የሚሰጠው ሙያዊ ድጋፍ ችግር ፈቺ አለመሆኑን፣

189. በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ የሪጅን፣ የቅ/ጽ/ቤቶችንና ባለድርሻ አካላትን እንደሚያሳትፍ፣ የፍላጎት ጥናት በማድረግ ለሰራተኞች የሚሰጥ ስልጠና በተመለከተ በኤጀንሲው በ 2008 አዲሱ የምዝገባ እና የመዋጮ የመረጃ አያያዝን በተመለከት በ 2009 ዓ.ም እንጂ ሌላ ስልጠና ያልተሰጠ እንደሆነ፣

190. በሪጅን ቅርንጫፍ ፅ/ቤታቸው ግን የስልጠና ፍላጎት ጥያቄ ለሰራተኛው በመስጠትና የስልጠና ተቋማትን በማነጋገር ስልጠና የሚሰጡ መሆኑን እናኤጀንሲው በሪጅንና በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የሚከናወኑና የሚሰጡ አገልግሎቶችን አፈፃፀም ገምግሞ በተገኙ ክፍተቶች ላይ ውይይት የሚደረግ ፣ ግብረ መልስ የሚሰጥ ሲሆን ሙያዊ ድጋፍ ግን

እንደማይደረግ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

191. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ኤጀንሲው ሁሉንም የሪጅንና ቅ/ፅ/ቤቶች ሃላፊዎች ቡድን መሪዎች ህዝብ ክንፍና ባለድርሻ አካላትን ባሣተፈ መልኩ ከ2008-2012 ስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ፣

192. በዕቅድ ላይ በዋናው መ/ቤት ሪጅኖችና ቅ/ፅ/ቤቶች በየደረጃው የማወያየትና ዕቅዱን የማዳበር ሥራ መሰራቱን፣ ለህዝብ ክንፍና ባለድርሻ አካላትም ረቂቅ ቀርቦ ሠፊ ውይይት የማድረግና ግበዓት የመሰብሰብ ስራ የተሰራ መሆኑን፣ ዓመታዊ ዕቅዱም በተመሳሳይ መልኩ ለውይይት እየቀረበና እየፀደቀ በመፈፀም ላይ እንደሚገኝ፣

193. የኤጀንሲው የሰው ሃይል ፍልሰት ከፍተኛ ከመሆኑም አንፃር በየጊዜው በሚለቁ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ምትክ አዲስ ለሚገቡት ከሥር ከሥር የማወያየትና ተመሣሣይ ግንዛቤ እንዲይዙ በማድረግ በኩል በየፅ/ቤቱ ውስንነት ቢኖርም እጀንሲው በእቅዱ ላይ ፅ/ቤቶችና ባለድርሻ አካላትን አያሣትፍም የሚለው ድምዳሜ ከተጨባጭ ሁኔታው አንፃር ትክክል አለመሆኑን የገለፁ ቢሆንም ማስረጃውን ለኦዲት ቡድኑ አላቀረቡም፡፡

194. እንዲሁም በሪጅኖችና ቅ/ጽ/ቤቶች የኃላፊና ሠራተኛውን ሙያዊ አቅም የሚያሣድጉ ስልጠናዎች በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ሲሰጡ መቆየቱን፣ ለምሳሌ በ2005/9 ስልጠናዎች በድግግሞሽ ለ265 2 ኃላፊና ሰራተኞች /በ2006/15 ስልጠናዎች ለ1436 ሀላፊና ሰራተኞች በ2007/8 ስልጠናዎች ለ602 ኃላፊና ሰራተኞች ፣ በአጠቃላይ ከ2005-2007 ብቻ በ32 የስልጠና ዓይነቶች በድግግሞሽ ለ4690 ኃላፊና ሰራተኞችን የአመራር ክህሎትና ሙያዊ አቅም ለማሰደግ መሆኑን፣ የበላይ አመራሩ በዓመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ ሪጅን ጽ/ቤቶችና በስራቸው የሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶችን በግንባር እየተገኘ ይገማገማል በታዩ ክፍተቶች ላይም የማስተካከያ አቅጣጫ እንደሚያስቀምጥ ቢገልፁም ማስረጃውን ለኦዲት ቡድኑ አላቀረቡም፡፡

195. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ማስረጃ ሳያቀርቡ ይህን ይበሉ እንጂ የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመለከታቸው ሪጅን ፣ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ እንደማያሳትፍ እና የፍላጎት ጥናት በማድረግ ለሰራተኞች የሚሰጥ ስልጠና የሌለ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ኤጀንሲው አገልግሎቶቹን በተጠናከረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርአትና የጡረታ ፈንዱን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በተሟላና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ አደራጅቶ መያዙን በተመለከተ፤

196. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

197. በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ ሪጅንና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲሁም ውክልና ከተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች ጋር ኔትወርክድ የሆነ አሠራር አለመኖሩ፣ የሰራተኛና የድርጅት ምዝገባ ሶፍትዌር አለመኖሩና በሪጅንና በሥራቸው ባሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፋይሎቻቸው ሰርቨር ላይ ባለመቀመጡ በባካፕ ስለሚያዙ ፋይሎቻቸው የተጠበቁ አለመሆኑ፣ በኤጀንሲው የሠራተኞች ሌጀር ከሐምሌ 2005 ዓ.ም ጀምሮ እንደነበረና ነገር ግን INSA /በኤጀንሲው እየሰራ ያለ ድርጅት/በፊት ከነበረው ሶፍትዌር ጋር ፊት ስላላደረገ በሚል ምክንያት መቋረጡ፣ እንዲሁም በኤጀንሲው እስከ 2006 ዓ.ም. የራሱ ድረ-ገጽ አለመኖሩ፣

198. የጡረታ መዋጮ ሶፍትዌር ባለመኖሩ የከፈሉትንና ያልከፈሉትን በቀላሉ ለማየት ባለመቻሉ የሥራ መጓተት መፍጠሩ ተገኝቶ ነበር፡፡

199. ኤጀንሲው ተገልጋዮች፣ ባለድርሻ አካላትና ፈጻሚ አካላት የጡረታ አዋጆች መመያዎችና ደንቦችን በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ፣ የጡረታ አመዘጋገቡና አሰባሰቡ ቀልጣፋ እንዲሆን የኢንፎሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ሊኖረው እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

200. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፈ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ክፍተቱን እስከ ታህሳስ 2008 ዓ.ም እንደሚተገበር ገልጿል፡፡

201. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

202. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ አገልግሎቶቹን በቅልጥፍናና በጥራት ለመስጠት የሚያስችሉ እና ከጽ/ቤቶቹና ከተገልጋዮች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ቢገልፁም አለመኖሩን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል ነገር ግን በዕቅዱ የተሸፈኑት የግል ድርጅቶችንና የሠራተኞችን የምዝገባ ማስረጃና የጡረታ ፈንዱን የሚመለከቱ ማስረጃዎችን በተሟላና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ተደራጅተው ለመያዝ የሚያስችል የአበል ምዝገባ /PRMS//PENTION REGISTRATION MANAGEMENET SYSTEM/ እና የጡረታ

መዋጮ/PSMS//PENSTION CONTRIBUTION MANAGEMENET SYSTEM/ የተባለ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን፣

203. በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የምዝገባ ማስረጃዎች ተመዝግበው የተያዙ ሲሆን የመዋጮውን መረጃ በየድርጅቱ መዝግቦ ለመያዝ የመለየት ስራ እየተሰራ ሲሆን በምዝገባና መረጃ አያያዝ ላይ የመረጃዎች ጥራት ማነስና ሙሉ ሆኖ አለመገኘት ችግሮች መኖራቸውን እና አገልግሎቶቹን በቅልጥፍናና በጥራት ለመስጠት የሚያስችሉ እና ከጽ/ቤቶቹና ከተገል,ጋዮች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ቢገልፁም አለመኖሩን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት መቻሉ፣

204. ነገር ግን በዕቅዱ የተሸፈኑት የግል ድርጅቶችንና የሠራተኞችን የምዝገባ ማስረጃና የጡረታ ፈንዱን የሚመለከቱ ማስረጃዎችን በተሟላና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ተደራጅተው ለመያዝ የሚያስችል የአበል ምዝገባ /PRMS//PENSION REGISTRATION MANAGEMENET SYSTEM/ እና የጡረታ መዋጮ /PSMS/ /PENSION CONTRIBUTION MANAGEMENET SYSTEM/ የተባለ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን፣

205. በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ፣ በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት ፣ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት እና በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ፅ/ቤት ከተገል,ጋዮች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት የሌለ መሆኑን፣ ነገር ግን መረጃዎችን ለመያዝ የሚያስችል የአበል ምዝገባ /PRMS/ /PENSION REGISTRATION MANAGEMENET SYSTEM/ እና የጡረታ መዋጮ /PSMS/ /PENSION CONTRIBUTION MANAGEMENET SYSTEM/ የተባለ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን፣

206. በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት አገልግሎቶቹን በቅልጥፍናና በጥራት ለመስጠት የሚያስችሉ እና ከጽ/ቤቶቹና ከተገል,ጋዮች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ስርዓት (ድረ-ገጽ፣ ኢ-ሜል...) ያልተዘረጋ እንደሆነ ፣

207. በዕቅዱ የተሸፈኑት የግል ድርጅቶችንና የሠራተኞችን የምዝገባ ማስረጃና የጡረታ ፈንዱን የሚመለከቱ ማስረጃዎች የተደራጁ ቢሆንም አስተማማኝነቱ ላይ ውስንነቶች ያሉ መሆኑን፣

208. የጡረታ መዋጮ ገቢ ላይ የሚመጡ መረጃዎች ጥራት የሌላቸው እና ጉድለት ያለባቸው ሲሆን በሌሎች ሪጅን ፅ/ቤቶች እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች እየተዘረጋ ያለው መረጃዎችን ለመያዝ የሚያስችል የአበል ምዝገባ /PRMS/ /PENSION REGISTRATION MANAGEMENET SYSTEM/ እና የጡረታ መዋጮ /PSMS/ /PENSION CONTRIBUTION MANAGEMENET SYSTEM/ የተባለ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ተግባራዊ አለመደረጉን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣

209. በወልቂጤ ፣በያቤሎ ፣ በወላይታ፣ በአርባምንጭ እና ፣ በሆሳዕና ቅርንጫ ፅ/ቤቶች የድርጅትና የሠራተኛ ምዝገባ ላይ ያልተሟሉ መረጃዎች መኖራቸውን፣ ምዝገባንና መዋጮን በዳታ ቤዝ የመመዝገብ ስራ ጥራትና ግልፅነት አለመኖሩን፣ ከኤጀንሲው በሪጅንና በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ከተደረገ የመስክ ምልከታ ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

210. የኤጀንሲው ፈንድና ኢንቨስትመንት ዳይሬክቶሬት የመረጃ አያያዝን በተመለከተ ለዳይሬክቶሬቱ ስራ በግብዓትነት ከተለያዩ የሪጅን ፅ/ቤት እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚደርሳቸው ፕሮሰስ የተደረጉ ስራዎች መረጃ በአግባቡ የሚያዝ ሲሆን የሚያዘውም በማንዋል መሆኑን የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

211. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ኤጀንሲው ሥራዎቹን በመረጃ ቴክኖሎጂ ማገዝና ዘመናዊ የዓሰራር ስረዓትን መከተል ለቅልጥፍናና ውጤታማነቱ ወሳኝ እንደሆነ በማመን እንደ አዲስ ተቋምነቱ በፍጥነት ወደ ስራ ገብቶ ብዙ ርቀት መጓዙን፣ በአሁኑ ሰዓት የሲስተም ማበልፀግ ሥራው ተጠናቆና ተመርቆ መረጃዎችን ወደ data base የማስገባት ሥራ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

ኤጀንሲው ለተገልጋዮችና ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠቱንና በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለይቶ የሚፈታበት ወጥ የሆነ መደበኛ የውይይት መድረክ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤

212. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

213. ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ የከፍተኛ ግብር ከፋይ በኤጀንሲው የግንዛቤ ማስጨበጫ ያልተሰጠው መሆኑ፣

214. በሪጅንና ቅ/ጫ/ጽ/ቤቶች በናሙና ከታዩ 12 የግል-ድርጅቶች ለአሥሩ የግል ድርጅት ግንዛቤ ማስጨበጫ ያልተሰጠ መሆኑ፣ ግንዛቤው የተሰጣቸው ሁለት የግል-ድርጅቶችም ኤጀንሲው ባዘጋጀው መድረክ ሳይሆን ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ባዘጋጀው መድረክ በመሆኑ በውይይቱ ላይ ለተነሱ ጥያቄዎች የሚፈለገው ማብራሪያ አለመሰጠቱ ተገኝቶ ነበር።

215. ኤጀንሲው ተገልጋዩች፣ ባለድርሻ አካላትና ፈጻሚ አካላት ስለ ጡረታ አዋጁ ጠቀሜታና በወጡ ጡረታ አዋጆች መመሪያዎችና ደንቦችን እንዲያውቁትና እንዲተገብሩት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም /በራሪ ወረቀቶችን በማዘጋጀት፣ የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም.../ በየአመቱ ግንዛቤ ሊሰጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

216. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ ደብዳቤ ቁጥር ገፈ 5.1/3/42/07 በቀን 05/07/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በሳምንትና በ15 ቀን በሬዲዮና ፣በጋዜጣ ዓምድ በቋሚነት ፣እንደአስፈላጊነቱ የምድረክ ገፅ ለገፅ ግንዛቤ ማስጨበጫ በማከናወን ላይ እንደሚገኝና በተከታታይ እንደሚሰራ ገልጿል፡፡

217. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

218. ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ለማወቅ እንደተቻለው፡

219. በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ እንደሚሰጥ፣ ስለተግባራዊነታቸውም ክትትል የሚያደርግ መሆኑን ፤ የውይይት መድረክ ከዚህ ቀደም መኖሩን አሁን ግን መቅረቱን፣

220. በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የግንዛቤ ማስጨበጫን በተመለከተ በገቢዎች ባለስልጣን የተለያዩ ባነሮችን በመስቀል እና በራሪ ፅሁፎችን በመበተን የግንዘቤ

ማስጨበጫ እንደሚሰሩ ነገር ግን በመድረክ የሚሰጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ በ 2009 ዓ.ም ያልተሰጠ መሆኑን፣

221. በደቡብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክን በተመለከተ በሪጅን ደረጃ ከገቢዎች ጋር የውይይት መድረክ ፣ ለግል ድርጅቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ተዘጋጅቶ የሚሰጥ መሆኑን፣

222. በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት የግንዛቤ ማስጨበጫን በተመለከተ ከ 2007 ዓ.ም ጀምሮ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ያልተዘጋጀ መሆኑን፣

223. ኤጀንሲው ለሆሳዕና ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን፣ ለሀዋሳ ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን፣ ለባህር ዳር አማራ ብድርና ተቋም ፅ/ቤት፣ በባህር ዳር አዶናስ ጠቅላላ ሆስፒታል ፣ በባህር ዳር ብሉ ናይል ኮሌጅ፣ ለባህር ዳር ግራንድ ሆቴል ለሚመለከታቸው ሰራተኞች በጡረታ መዋጮ ጠቀሜታና ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ በወጡ መመሪያዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰጥቶ እንደማያውቅ፣

224. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት፣ በደብረማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት፣ በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቅ/ፅ/ቤት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ የሚሰጥ እንደሆነ፣ ስለተግባራዊነታቸውም ክትትል የሚያደርግ መሆኑን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ቢገልፁም ማስረጃው አልቀረበም፡፡

225. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ኤጀንሲው ከአዋጅ ጋር በተያያዙ ርዕሶች ላይ በተለይም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠቱን፣ ከ2007 በኋላ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራውን እንዲቀጥል ሆኖ በዋነኛነት የህግ ማስገደድ ሥራው ላይ ማቶከር እንዳለበት አቅጣጫ ተቀምጦ ሲተገበር መቆየቱን፣ ለምሳሌ ከ2004-2007 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባና በተለያዩ ክልሎች 677 የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተፈጥረው ለባለድርሻ አካላት አዋጅና አፈፃፀም መመሪያውን የማስረዳትና ግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ የተሰራ መሆኑን የገለፁ ቢሆን ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

226. እንዲሁም በየቦታው የኃላፊዎችና ሠራተኞች መቀያየር ፈጣን በመሆኑ በኦዲት ግኝቱ እንደተጠቀሰው ግንዛቤ ያላገኙ ሠራተኞችና ኃላፊዎች መኖራቸውን፣ የግንዛቤ

ማስጨበጫ ሥራው ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ክፍተቱ እየተደፈነ የሚሄድ እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

227. በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አሰባሰብ ፣ አስተዳደርና አከፋፈል ብቃት ያለው ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

3.1. እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ✓ በኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ የሚቋቋምበት የህግ ማዕቀፍ ፣ የፈንድ አስተዳደር ማንዋል እና የጸደቀ የሂሣብ አያያዝ ማንዋል እንዲኖር መደረጉ፣
- ✓ በናሙና በታዩ ሪጅንና ቅ/ጽ/ቤቶች የግል ድርጅቶች በአዋጁ መሠረት በትክክል ስለመክፈላቸውም ሆነ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ስለመሰብሰቡ በቂ ባይሆንም ኦዲት የሚደረግ መሆኑ፣
- ✓ ኤጀንሲው ዘመናዊ የጡረታ መዋጮ ምዝግባ /PRMS/ /PENSION REGISTRATION MANAGEMENET SYSTEM/ እና የመዋጮ /PCMS/ /PENSION CONTRIBUTION MANAGEMENET SYSTEM/ የተባለ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ እየተገበረ መሆኑ፣
- ✓ ኤጀንሲው በሪጅኖች ፣ ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ግምገባ በማድረግ ግብረ መልስ የሚሰጥ መሆኑ፣

መኖሩ ታውቋል፡፡

3.2. እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- ኤጀንሲው በክዋኔ ኦዲት ወቅት የተገኙ ክፍተቶችን እና የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦችን ሪፖርት ለሚመለከታቸው የሪጅን እና የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ሃላፊዎች አለማሳወቅ፣
- በኤጀንሲው የግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ አለመቋቋሙ፣

- በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ በማህበራዊ ዋስትና የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞች ብዛትን ለማወቅ የሚያስችል በኤጀንሲው የተጠና ጥናት አለመኖሩ፣
- የግል ድርጅቶችን በጡረታ ዐቅዱ ለመሸፈን ከ2003-2007 ዓ.ም. በስትራቴጂክ ዕቅድ የግል ድርጅቶች የምዝገባ ዕቅድ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው እያንዳንዱ የግል ድርጅት የሠራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደመወዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ በየወሩ በትክክል ስለመክፈሉ እስከ ወረዳ ድረስ የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት የተዘረጋ ውጤታማ የአሰራር ስርአት የሌለው መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅዱ የተሸፈኑ የግል ድርጅቶችን አዋጁ ባስቀመጠው መሰረት በተሟላ ሁኔታ በየወሩና በትክክል እንዲከፍሉ ያላደረገ መሆኑ፣
- የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ሂሳብ በኤጀንሲው ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ አካላት በአዋጁ መሰረት በትክክል ገቢ ማድረጋቸውን እና በውሉ መሰረት እየሰሩ ስለመሆኑ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር በበቂ ደረጃ አለመደረጉ፣
- በኤጀንሲው ከግል ድርጅቶች ተሰበሰበው ወደ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወቅቱ ሳይተላለፉ የሚዘገዩ እና ከየት እንደተሰበሰቡ የማይታወቁ የጡረታ መዋጮ ሂሣቦች መኖራቸው፣
- ወጥ የሆነ የጡረታ መዋጮ አሰባሰበ የሌለ መሆኑ (በአዲስ አበባ ውክልና በተሰጣቸው የገቢ ሰብሳቢ ጽ/ቤቶች ሲሰበሰብ በሪጅንና ቅ/ጫ/ጽ/ቤች ደግሞ የግል ድርጅቶቹ የጡረታ መዋጮ ሂሳባቸውን ራሳቸው በቀጥታ ወደ ጡረታ መዋጮ ባንክ አካውንት የሚያስገቡ መሆኑ)፡
- በናሙና በታዩ ሪጅንና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የሂሳብ መዝገብ በማይዙ እና መረጃ በማይሰጡ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ የተደራጀ ፣ የተሟላና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ አለመኖሩና ግዴታቸውን ባልተወጡ የግል ድርጅቶች ላይ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ከመፃፍ የዘለለ እርምጃ እየተወሰደ አለመሆኑ፣

- ጡረታ መዋጮ ፈንዱን ለማዳበር የጡረታ መዋጮውን አሟጦ በመሰብሰብ ትርፋማ እና ውጤታማ በሆኑ ኢቨንስትመንቶች ላይ ለማዋል በጥናት ላይ የተመሰረተ እቅድ አለመኖሩ፣
- ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ገቢን ሲያቅድ የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን በመሰብሰብና የሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ ሳይሆን በግምትና የጡረታ መዋጮ በየዓመቱ ስለሚጨምር ይጨምራል በሚል መነሻ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮውን ለማዳበር በወቅቱ አሟጦ የማይሰበስብ መሆኑ እንዲሁም የጡረታ ፈንዱንም በትሬዠሪ ቦንድ ሽያጭ ላይ ብቻ የሚያውልና ሌሎች አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች በማዋል በተጨማሪ ማግኘት ያለበትን ትርፍ እያገኘ አለመሆኑ፣
- ኤጀንሲው ሲያቅድ ሪጅን፣ ቅ/ጽ/ቤቶችን እና ባለድርሻ አካላትን የማያሳትፍ ሲሆን ሪጅኖች፣ ክልሎችና የአዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትል በማድረግ የሚታዩ ክፍተቶች ላይ ሚያዊ ድጋፍ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ውክልና ለሰጣቸው የገቢ ጽ/ቤቶችም ሆነ ለፈፃሚ አካላት የፍላጎት ጥናት በማድረግ አስፈላጊውን ስልጠና የማይሰጥና አዲስ ለሚቀጠሩ ሠራተኞችም ምንም አይነት ስልጠና ሳይሰጥ ወደ ሥራ እንዲገቡ የሚደረግ መሆኑ፣
- በኤጀንሲ ጠንካራ የሆነ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት አለመኖር፣
- ኤጀንሲው ለተገልጋዮችና ለባድርሻ አካላት በሚፈለገው መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ያልሰጠ መሆኑ፣

እስካሁን መኖሩ ታውቋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

228. በመጀመሪያው የክዋኔ ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡

229. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ባልተስተካከሉና የእርምት እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና በናሙና የታዩት የጡረታ አበል ሰበሳቢ ፣ ከፋይ እና የግል ድርጅቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

በደብረ ማርቆስ ቅ/ፅ/ቤት ከሀምሌ 2008ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30/2009 ዓ.ም በግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ እዳ ያለባቸው የግል ድርጅቶች

ተ.ቁ	የድርጅቱ ስም	የሚገኝበት ወረዳ	በኦዲት ምርመራ የተገኘ ውዝፍ እዳ		በወቅቱ ባለመከፈል				ድምር		የሰነድ ማስረጃ የቀረበበት እዳ		ተከፍሎ የክፍያ መረጃ የቀረበበት እዳ		ቀሪ እዳ	
					5 ከመቶ ቅጣት		የባንክ ወለድ									
			ብር	ሳ	ብር	ሳ	ብር	ሳ	ብር	ሳ	ብር	ሳ	ብር	ሳ	ብር	ሳ
1	ተስፋ ማህበረሰብ ልማት አቀፍ ምህበር	ደ/ማ	80,453	26	60,339	90	5,028	30	145,821	46	139,771	46	-	-	6,050	00
2	ሂውማን ብሪጅ ባዮ ሜዲካል ኮሌጅ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ደ/ማ	313,434	20	90,742	12	7,561	85	411,738	17	279,786	60	-	-	86,502	37
3	ግሎሪ ሆቴል	ደ/ማ	9,046	10	8,368	59	697	38	18,112	07	1,769	00	5,000	00	11,343	07
4	ሳትኮን ፈለገ ጊዮን መንገድ ስራ ድርጅት	እነማይ	-	-	-	-	-	-	4,392,988	54	-	--	2,696,494	27	1,696,494	27
	ድምር		402,933	56	159,450	61	13,287	53	4,968,660	17	421,327	06	2,701,494	27	1,800,389	81

አባሪ 2

በኤጀንሲው በግንቦት ወር 2009 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው የግል ድርጅቶች

ተ.ቁ	የድርጅቱ ስም	ተሰብሳቢ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	ባለፉት ወራት የተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ ዋጫ	በግንቦት ወር 2009 ዓ.ም የተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	ቀሪ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	ውዝፍ የጡረታ መዋጮውን የጠየቀው ሪጅን/ቅ/ፅ/ቤት
1	ኢዲኬ ጀሶና ኖራ ፋብሪካ ኃ.የተ.የግ.	41,809.09	0.00	0.00	41,809.09	አምቦ
2	አምቦ አብዲ ኬኛ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት	65,798.24	**0.00**	0.00	65,798.24	አምቦ
3	ኬን ኮንሰልታንት ኃ.የተ.የግ.ማ	332,954.95	598.47	0.00	332,356.48	ዋና መ/ቤት
4	አይጠገብ ካፌና ሬስቶራንት	129,630.06	2,966.25	17,011.03	109,652.78	ኮምቦልቻ
5	አቢ.ትሜክ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ ማ	25,520.00	0.00	0.00	25,520.00	ዋና መ/ቤት
6	Adiamat garage plc	56,184.98	444.68	0.00	55,740.30	ዋና መ/ቤት
7	ለይኩን ቢዝነስ	341,608.78	39,914.87	0.00	301,693.91	ዋና መ/ቤት
8	ኮክ ከረሜላ ኃ.የተ.የግ.ማ	213,159.09	386.50	0.00	212,772.59	ዋና መ/ቤት
9	ሼድ ጄነራል ኮንስትራክሽን	1,912,671.73	1,328,974.46	0.00	583,697.28	መቱ
10	ሀዋሳ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር	533,466.42	268,007.40	381,668.83	265,459.02	ሃዋሳ
11	ኤች ፒ ጋውፍ ኢንጂነሪንግ	481,582.84	481.29	0.00	481,101.55	ዋና መ/ቤት
12	ሊዮን ቱር እና ትራቭል	21,786.39	0.00	0.00	21,786.39	ዋና መ/ቤት
13	አቶ ቴድሮስ አዱሱ	85,531.77	665.85	0.00	84,865.92	ጅግጅጋ
14	አቶ ሆደን ኡስማን	19,526.40	0.00	0.00	19,526.40	ጅግጅጋ
ተ.ቁ	የድርጅቱ ስም	ተሰብሳቢ ውዝፍ የጡረታ	ባለፉት ወራት የተሰበሰበ	በግንቦት ወር 2009 ዓ.ም	ቀሪ ውዝፍ የጡረታ	ውዝፍ የጡረታ

		መዋጮ	ውዝፍ የጡረታ ዋጫ	የተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	መዋጮ	መዋጮውን የጠየቀው ሪጅን/ቅ/ፅ/ቤት
15	ሰላማዊት አሻግሬ	3,521.72	0.00	0.00	3,521.72	ጅግጅጋ
16	ፈሪድ አደም	70,686.25	137,500.00	0.00	56,936.25	ጅግጅጋ
17	አህዱ ቴክ አይሲቲ ሶሊሽን	1,603.33	0.00	0.00	1,603.33	ጅግጅጋ
18	አሚና ሬስቶራንት	11,002.82	0.00	0.00	11,002.82	ጅግጅጋ
19	አራርሶ ሆቴል	2,526.22	0.00	0.00	2,526.22	ጅግጅጋ
20	ፒስ የወንዶች የውበት ሳሎን	693.6	0.00	0.00	693.6	ጅግጅጋ
21	ሪች ጀነራል ቢዝነስ	183,113.96	2,798.87	0.00	180,315.09	ዋና መ/ቤት
22	ተወከል ካፌ	7,887.60	0	0.00	7,887.60	ጅግጅጋ
23	ትራንስ ናሽናል ኮምፒውተር	1,267,985.05	0	0.00	1,267,985.05	ዋና መ/ቤት
24	ወንድሙ ከፍተኛ ክሊኒክ	9,510.60	0	0.00	9,510.60	ጅግጅጋ
25	ዳል ሱር ሱፐር ማርኬት	16,762.00	421.22	0.00	16,340.78	ጅግጅጋ
26	ኢስትሆሪዞን ኮነሰልታንት	20,182.00	0	0.00	20,182.00	ጅግጅጋ
27	ድሬ ነርሲንግ ሆም ኬር ክሊኒክ	17,064.26	0	0.00	17,064.26	ጅግጅጋ
28	ኢፍቲን የምግብ አቅርቦትና ወላጅ አ	31,828.55	0	0.00	31,828.55	ጅግጅጋ
29	ሃርላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ	38,018.88	1,872.19	2,271.77	33,874.92	ዋና መ/ቤት
30	ሀፒ የወንዶች ፀጉር ቤት	3,536.40	0.00	0.00	3,536.40	ጅግጅጋ
31	አሳት ኮ ጉምሩክ አስመጪ	26,914.00	0.00	0.00	26,914.00	ጅግጅጋ
32	9 ሲስተር ካፌ እና ሬስቶራንስ	27,666.68	0.00	0.00	27,666.68	ጅግጅጋ
33	ወደኒየአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ	56,422.24	0.00	0.00	56,422.24	ጅግጅጋ
ተ.ቁ	የድርጅቱ ስም	ተሰብሳቢ ውዝፍ የጡረታ	ባለፉት ወራት የተሰበሰበ	በግንቦት ወር 2009 ዓ.ም	ቀሪ ውዝፍ የጡረታ	ውዝፍ የጡረታ

		መዋጮ	ውዝፍ የጡረታ ዋጫ	የተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	መዋጮ	መዋጮውን የጠየቀው ሪጅን/ቅ/ፅ/ቤት
34	አሚራ አድን ሬስቶራንት	27,577.24	0.00	0.00	27,577.24	ጅግጅጋ
35	ከሰም ትራንስፖርት አ.ማ	3,919.13	3,650.92	0.00	268.21	ጅግጅጋ
36	ሳቢር ፈርኒቸር	6,403.52	0.00	0.00	6,403.52	ጅግጅጋ
37	በዴ ሆቴል	9,100.80	0.00	0.00	9,100.80	ጅግጅጋ
38	ታዬ መዳኒት ና ሕክምና ማእከል	11,865.13	0.00	0.00	11,865.13	ጅግጅጋ
39	ቢ.ቃ ኮንስትራክሽን	5,386.52	0.00	0.00	5,386.52	ጅግጅጋ
40	ወሎ ሆቴል	2,635.20	0.00	0.00	2,635.20	ጅግጅጋ
41	ኤሊያስ ሆቴል	9,244.78	0.00	0.00	9,244.78	ጅግጅጋ
42	ማዕዘን አጠቃላይ ንግድ ፒ ኤል ሲ	297,023.53	33,668.98	0.00	263,354.55	ዋና መ/ቤት
43	መናሀሪያ ግሮሰሪ	1,408.50	571.99	0.00	836.51	ጅግጅጋ
44	ጻድቃኔ ሆቴል	754.20	490.00	0.00	264.2	ጅግጅጋ
45	ማስተር ዲጂታል እስቱዲዮ	1,846.14	192.82	0.00	1755.22	ጅግጅጋ
46	ኡመር ቡክር ስቱዲዮ	13,673.48	0.00	0.00	13,673.48	ጅግጅጋ
47	ኩልምዬ መድሃኒት	2,126.25	0.00	0.00	2,126.25	ጅግጅጋ
48	ሶዶ ምንጭ ግሮሰሪ	1,476.90	0.00	181.25	1,476.90	ጅግጅጋ
49	ወደኔ ካፌና ሬስቶራንት	1,737.45	0.00	0.00	1,737.45	ጅግጅጋ
50	ፍሮምሳ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች	1,476.90	0.00	0.00	1,476.90	ጅግጅጋ
51	ሂማሎ የህትመት ስራ	2,517.75	0.00	0.00	2,517.75	ጅግጅጋ

ተ.ቁ	የድርጅቱ ስም	ተሰብሳቢ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	ባለፉት ወራት የተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ ዋጪ	በግንቦት ወር 2009 ዓ.ም የተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	ቀሪ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	ውዝፍ የጡረታ መዋጮውን የጠየቀው ሪጅን/ቅ/ፅ/ቤት
52	ነዲራ የባህል ምግቦች	6,949.80	387.64	0.00	6,562.16	ጅግጅጋ
53	አዲስ ህይወት ማህበረሰብ ድርጅት	1,225,312.19	544,258.00	0.00	681,054.19	ዋና መ/ቤት
54	ሆርሴድ የህንጻ መሳሪያ	2,551.50	0.00	0.00	2,551.50	ጅግጅጋ
55	አብዱቀኒ ኤሌክትሮኒክስ	579.15	0.00	0.00	579.15	ጅግጅጋ
56	መገናኛ ግሮሠሪ	637.87	0.00	0.00	637.87	ጅግጅጋ
57	ዴክስ ዳቦ ማምረቻ	14,769.00	0.00	0.00	14,769.00	ጅግጅጋ
58	ራያን መዳኒት መደብር	11,610.00	0.00	0.00	11,610.00	ጅግጅጋ
59	ሂሩት መታሠቢያ ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/ የግ /ማ	20,803.27	0.00	0.00	20,803.27	ሃዋሳ
60	አፍሮ አምላክ ሶላርቴክ ኃ/የተ/የግ/ማ	63,092.52	0.00	20,000.00	43,092.52	ዋና መ/ቤት
61	አፍሪካ ባንቦ ኃ/የተ/የግ/ማ	752,224.02	0.00	0.00	752,224.02	ዋና መ/ቤት
62	ኢቴኮ ፒ. ኤል. ሲ	1,258,487.08	44,713.98	0.00	1,213,773,1	ሃዋሳ
63	ቴሲ ኢንጂነሪንግ	1,382,752.03	0.00	646,682.02	736,070.01	ኮምቦልቻ
64	ውብርስት ህትመት	563,645.66	1,864.38	0.00	561,781.28	ሃዋሳ
65	ማውንት ኦሊቭ ት/ቤት	1,116,493.93	1,679.00	0.00	1,097,814.93	ሃዋሳ
66	ያማሬ ካፌና ሬስቶራንት	392,883.13	17,222.91	0.00	388,673.93	ሃዋሳ
67	ማይ ፌበራይት ካፌና ሬስቶራንት	232,336.34	0.00	0.00	232,336.34	ሃዋሳ
68	ኤስ ደብሊው ኤስ ኮንስትራክሽን	1,500,773.02	0.00	0.00	1,500,773.02	ወልዲያ

ተ.ቁ	የድርጅቱ ስም	ተሰብሳቢ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	ባለፉት ወራት የተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ ዋጫ	በግንቦት ወር 2009 ዓ.ም የተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	ቀሪ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ	ውዝፍ የጡረታ መዋጮውን የጠየቀው ሪጅን/ቅ/ፅ/ቤት
69	አመል ኮንስትራክሽንሃ/የተ/የግ/ማ	115,532.60	0.00	0.00	115,532.60	ዋና መ/ቤት
70	ሱፐር ሊትል ፍላወር ኃ/የተ/የግ/ማ	76,889.22	0.00	20,000.00	56,889.22	ዋና መ/ቤት
	ጠቅላላ ድምር	17,606,052.63	2,442,044.52	3,366,870.49	11,920,887.62	

አባሪ 3.

<u>በሰሜን አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ2008ዓ.ም ወደ ብሄራዊ ባንክ ያልተላለፈ የገንዘብ መጠን</u>

ተ.ቁ	አራዳ ክ/ከተማ	በወሩ የተሰበሰበ	ወደ ብሄራዊ ባንክ የተላለፈ	ወደ ብሄራዊ ባንክ ያልተላለፈና በባንክ የሚገኝ
1	ሐምሌ 2007	1,838,021.77	939,800.00	898,221.77
2	ነሃሴ 2007	1,825,123.33	1,004,415.89	
3	መስከረም 2008	1,717,456.30	1,861,000.70	
4	ጥቅምት 2008	1,903,617.27	1,187,070.28	
5	ህዳር 2008	2,097,659.97	2,535,601.30	
6	ታህሳስ 2008	1,804,100.41	2,691,971.13	
7	ጥር	1,414,571.36	1,692,454.77	
8	የካቲት	2,099,725.58	1,858,353.31	
9	መጋቢት	2,401,654.79	1,933,700.31	
10	ሚያዚያ	2,201,450.94	1,998,430.93	
11	ግንቦት	1,335,573.00	2,031,142.07	
12	ሰኔ	1,717,122.03	2,796,378.30	
	ድምር	<u>22,356,076.75</u>	<u>22,530,318.99</u>	<u>(174,242.24)</u>

ተ.ቁ	ጉለሌ	በወሩ የተሰበሰበ	ወደ ብሄራዊ ባንክ የተላለፈ	ወደ ብሄራዊ ባንክ ያልተላለፈና በባንክ የሚገኝ
1	ሐምሌ 2007	719,440.48	359,459.88	
2	ነሃሴ 2007	687,984.36	379,723.45	
3	መስከረም 2008	627,973.12	223,007.22	
4	ጥቅምት 2008	782,548.76	670,519.20	
5	ህዳር 2008	828,741.30	766,923.55	
6	ታህሳስ 2008	793,399.03	565,164.06	
7	ጥር	744,054.03	1,328,195.80	
8	የካቲት	771,551.57	986,580.54	
9	መጋቢት	759,732.38	753,113.19	
10	ሚያዚያ	842,512.35	522,033.76	
11	ግንቦት	910,419.56	871,751.32	
12	ሰኔ	990,093.23	620,334.69	
	ድምር	9,458,450.17	8,082,746.66	1,375,703.51

ተ.ቁ	አዲስ አበባ ቁ.1	በወሩ የተሰበሰበ	ወደ ብሄራዊ ባንክ የተላለፈ	ያልተላለፈና በባንክ የሚገኝ
1	ሐምሌ 2007	3,291,515.15	6,624,139.36	
2	ነሃሴ 2007	12,324,453.38	3,874,667.47	
3	መስከረም 2008	8,353,331.24	10,949,661.19	
4	ጥውምት 2008	9,577,229.90	3,682,247.64	
5	ህዳር 2008	9,737,165.37	5,198,389.21	
6	ታህሳስ 2008	10,094,539.99	7,583,119.77	
7	ጥር	8,924,110.34		

8	የካቲት	9,308,469.48	18,734,706.70	
9	መጋቢት	8,733,876.69	17,527,968.81	
10	ሚያዚያ	9,223,507.76	3,291,561.17	
11	ግንቦት	9,559,152.29	18,303,813.96	
12	ሰኔ	9,155,095.78	10,669,782.70	
	ድምር	**108,282,447.37**	**106,440,057.98**	**1,842,389.39**
	ጠቅላላ የዓመቱ ድምር	**140,096,974.37**	**137,053,123.63**	**3,043,850.66**